ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 279 ሰኔ 9 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# ሕዝበ ሙስሊሙ የኢድ አል አድሃ በዓልን ሲያከብር ያለውን በማካፈል መሆን ይኖርበታል

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- ሕዝበ ሙስሊሙ የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓልን ሲያከብር በሃይማኖቱ አስተምህሮ መሠረት የተቸገሩ ወገኖችን በማሰብና ያለውን በማካፈል መሆን እንዳለበት የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት አስታወቀ።

ምክር ቤቱ በትናትናው ዕለት የአንድ ሺህ 445ኛ የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓልን በማስመልከት በአዲስ አበባና በመላው ዓለም ለሚገኙ የእስልምና እምነት ተከታዮች የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፏል።

የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼክ ሱልጣን አማን ኤባ ባስተላለፉት መልዕክት፤ የኢድ አል አድሃ(አረፋ) በዓል የመተሳሰብና የደስታ በዓል በመሆኑ ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከብር የተቸገሩ ወገኖቹን በማሰብና ያለውን በማካፈል ሊሆን ይገባል።

የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል ከፆምና ፀሎት ሃይማኖታዊ ሥርዓት በኋላ የሚከናወንና በእስልምና ሃይማኖት ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠው መሆኑን አስታውቀዋል።

ሕዝበ ሙስሊሙ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል

## በአረፋ በዓል የሚታየው መደጋገፍ እንዲጎለብት ሕዝበ ሙስሊሙ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- የአረፋ በዓል መገለጫ የሆነው መደጋገፍና መረዳዳት እሴት እንዲጎለብት ሕዝበ ሙስሊሙ ሃይማኖታዊ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል ሲሉ

በአረፋ በዓል...ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## “የዒድ አል አድሃ በዓል ማንኛውም ፈተና በጽናት ካለፉት ዋጋው ከፈተናው በላይ መሆኑን እንማርበታለን”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የዒድ አል አድሃ በዓል ማንኛውም ፈተና በጽናት ካለፉት ዋጋው ከፈተናው በላይ መሆኑን እንማርበታለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ለ2016 የዒድ አል አድሃ በዓልን አስመልክተው ትናንት ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት እንዳሉት፤

የኢድ አል አድሃ በዓል የፈተናና የመሥዋዕትነት በዓል ነው። ነቢዩ ኢብራሂም በአላህ ትእዛዝ ልጃቸውን ለመሥዋዕትነት ያዘጋጁበት፤ ጽናታቸው ተፈትኖ ያሸነፉበት በዓል ነው። ከዚህ በዓል የምንማራቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ማንኛውም ፈተና በጽናት ካለፉት ዋጋው ከፈተናው በላይ መሆኑን እንማርበታለን።

“የዒድ አል አድሃ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል




















# የትብብር ማዕቀፍ ስምምነቱን ተግባራዊ በማድረግ ቀጣናዊ እድገትን ማፋጠን ያስፈልጋል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የናይል ትብብር ማዕቀፍ ስምምነትን በፍጥነት ወደ ተግባር እንዲገባ በማድረግ ቀጣናዊ ትብብርና እድገት ማፋጠን አስፈላጊ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ አስታወቁ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት በመተባበር ‹‹የጋራ ሀብት ለጋራ መጻኢ ጊዜና ለጋራ ብልጽግና›› በሚል መሪ ሃሳብ ሦስተኛው ዙር ዓመታዊ የናይል ወንዝ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትና ቀጣናዊ ትስስር ጉባኤ ተካሂዷል።

በጉባኤው ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ እንደገለጹት፣መድረኩ በናይል ወንዝ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትና በተፋሰሱ ሀገራት መካከል ትብብርን ለማሳደግ ይረዳል። የናይል ውሃን በፍትሐዊነት ለመጠቀም በተፋሰሱ ሀገራት መካከል ትብብር ማጠናከር ተገቢ ነው።

የናይል ተፋሰስ ሀገራት በጋራ መልማት፣ የአየር ንብረት ለውጥን ተጽእኖን መቀነስ እንዳለባቸው አመልክተው፤ በተፋሰሱ ሀገራት መካከል የልምድ ልውውጥ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የዓባይ ግድብ ግንባታ የፍትሐዊ ተጠቃሚነት መርህን ባከበረ መልኩ እየገነባች ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ግድቡ በቀጣናው አንድነትና ቀጣናዊ መግባባትን ያጠናክራል። አባል ሀገራት የናይል የትብብር ማእቀፉን (CFA) ለማፅደቅ ትልቅ ዋጋ ሊሰጡ ይገባል። የትብብር ማዕቀፍ ስምምነቱ በፍጥነት ወደ ተግባር እንዲገባ መሥራት ለቀጣናው ትብብርና እድገት መሥራት ተገቢ ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ ማዕቀፉ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ አይነተኛ መንገድ ነው።



የናይል ተፋሰስ ኮሚሽን ለማቋቋም አባል ሀገራት የናይል የትብብር ማእቀፉን (CFA) ማፅደቅ እንዳለባቸው በቅርቡ ቡሩንዲ ማጽደቋን በመግለጽ፤ በቀጣይ አንድ አባል ሀገር ካጸደቀ ኮሚሽኑ የሚቋቋም ይሆናል።

የናይል ወንዝን ፍትሐዊና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ለመጠቀም የጋራ ጥረት ያስፈልጋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ለዚህም በሦስተኛው ጉባኤ ላይ ለመመካከር ከናይል ወንዝ የተፋሰስ ሀገራት የተውጣጡ ባለሙያዎች መሳተፋቸውን ገልጸዋል።

በአባል ሀገራት መካከል ትስስርንና የጋራ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ አባል ሀገራቱ ቁርጠኛ መሆን እንዳለባቸው አመልክተው፤ እያደገ የመጣውን የሕዝብ ብዛት ለመመገብ፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር፣ የውሃ ምንጮችን ለማጎልበትና የደን መጨፍጨፍን ለመጠበቅ በጋራ መሥራት አስፈላጊ ነው። የባለሙያዎችን ትብብር በማጠናከር የጋራ ተጠቃሚነትን ማሳደግ ሌላው ጠቃሚ ጉዳይ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር አቶ ጃፋር በድሩ በበኩላቸው፣ ጉባኤው በዓባይ ተፋሰስ ሀገራትና ማህበረሰብ መካከል ፍትሐዊ የውሃ ተጠቃሚነት እንዲኖር ያደርጋል። ኢትዮጵያ የናይል ትብብር ማእቀፍን በመፈረም አህጉራዊ ውህደትና የጋራ ተጠቃሚነት እንዲኖር ቁርጠኝነቷን አሳይታለች። ሌሎች ሀገራትም የኢትዮጵያን መንገድ በመከተል የናይል የትብብር ማእቀፉን ማጽደቅ አለባቸው ሲሉ አስገንዝበዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ጉባኤው እ.ኤ.አ ከ2022 ጀምሮ በተፋሰሱ ሀገራት መካከል እየተካሄደ ነው። በዚህም የቀጣናውን የኢኮኖሚ ውህደትና የፖለቲካ መረጋጋት እንዲመጣ ማድረግ ተችሏል።

ጉባኤው የአባል ሀገራት ምሁራን በናይል ወንዝ ፍትሐዊና ምክንያታዊ ድርሻ ላይ ተሰባስበው ፍሬያማ ውይይት እንዲያደርጉ ይረዳል ብለዋል።

# በመጪው ዓመት ከውጭ የሚገባ ሴራሚክስን በሀገር ምርት ለመተካት ታቅዷል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በ2017 በጀት ዓመት ከውጭ የሚገባውን ሴራሚክስ በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት እቅድ መያዙን የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽንና ካም ሴራሚክስ ማህበር የአክሲዮን ፊርማ ሥነሥርዓት ባካሄዱበት ወቅት የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ ባስተላለፉት የሥራ መመሪያ እንደገለጹት፣ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ለጥቅል ሀገራዊ እድገት ያለው አበርክቶ ከሰባት በመቶ ያነሰ ነው።

እንደ አቶ ታረቀኝ ገለጻ፤ መንግሥት ቅድሚያ ሰጥቶ ከሚሠራቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ የሴራሚክስ ምርትን ማሳደግ በመሆኑ ካም ሴራሚክስ በአጭር ጊዜ ወደ ምርት በመግባት ከውጭ የሚገባውን ምርት በሀገር ምርት መተካት ያስፈልጋል። የሴራሚክስ ምርት በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት ዕቅድ ተይዟል።

በሚቀጥለው ዓመት ሴራሚክስ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት በመንግሥት በኩል እቅድ አለ፤ ይህ ስምምነትም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ብለዋል።

መንግሥት የኢንዱስትሪው ዘርፍ እንዲያድግ ምቹ ፖሊሲዎችን አጽድቋል። የጸደቁት የፖሊሲዎች ዋነኛ አላማቸው በግሉ ዘርፍና በሽርክና የሚመራ የኢንዱስትሪ ሥርዓት እንዲገነባ ለማድረግ ነው ያሉት አቶ ታረቀኝ፤ በሽርክና የሚሠሩ ሥራዎች ከቀጣይነትና ከአትራፊነት አንጻር ትልቅ ቦታ ያላቸው በመሆኑ በትኩረት እንደሚሠራ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በሴራሚክስ ምርት የውጭ ጥገኛ ናት ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ እንደ ሀገር ያሉት ሁለት ኢንዱስትሪዎችም በውጭ ዜጋ የተያዙ ናቸው። ካም ሴራሚክስ የመጀመሪያው የሀገር በቀል በሽርክና የተጀመረው የሴራሚክስ ኢንዱስትሪ ነው። መንግሥት



ትኩረት ከሰጠባቸው ከተኪ ምርት አኳያ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ እየተሠራ ነው። የመንግሥትን ዓላማ ከማሳካት አንጻር ስምምነቱ ጉልህ ሚና አለው፤መንግሥታዊ ፕሮጀክት በመሆኑ የቅርብ ክትትል እንደሚደረግለትም ገልጸዋል።

በፊርማ ሥነሥርዓት ወቅት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዮናስ አያሌው (ኢንጂነር) እንደገለጹት፣ የካም ሴራሚክስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አጠቃላይ ካፒታል 2 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ነው። ከዚህ ውስጥ 30 በመቶ የአክሲዮን ድርሻውን የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ገዝቶታል ብለዋል።

ከካም ሴራሚክስ ጋር ስምምነት ላይ ለመድረስ ከአንድ ዓመት ከአምስት ወር በላይ መውሰዱን አመልክተው፤ ስምምነቱ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ያለበትን ችግር እንደሚቀርፍ ገልጸዋል።

የካም ሴራሚክስ ምርቶች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አስኪያጅ ዋሪዮ ጋልጋሎ በበኩላቸው፤ እንደ ሀገር ለሴራሚክስ ምርት ቅድሚያ በመስጠት ከውጭ የሚገባውን ምርት በሀገር ውስጥ መተካት ያስፈልጋል። የፕሮጀክቱ ግንባታ ላለፉት ሰባት ዓመታት በኮቪድ ፣በውጭ ምንዛሪ እጥረትና ከመሬት ጋር በተያያዘ ችግር የተጓተተ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ተጠናቆ ወደ ሥራ ይገባል ብለዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ ካም ሴራሚክስ ቢሾፍቱ ከተማ የሚገኘው ፕሮጀክት ነው። ከሦስት ወራት በኋላ ወደ ሥራ ይገባል። ሲጠናቀቅም የማምረት አቅሙ በቀን 20 ሺህ ካሬ ሜትር ሴራሚክ ይሆናል፤ ይህም አቅርቦትና ፍላጎት በዘላቂነት ሚዛናዊ እንዲሆን ይረዳል። ከውጭ የሚገባውን ምርት በሀገር ውስጥ በመተካት የሀገር ኢኮኖሚን ለማሳደግ ይረዳል።

# ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን አንድነቱንና ወንድማማችነቱን በማጠናከር እንዲያከብር ርዕሳነ መስተዳድሮች ገለጹ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን አንድነቱንና ወንድማማችነቱን በማጠናከር እንዲያከብር ርዕሳነ መስተዳድሮች ገለጹ። የክልሎች ርዕሰ መስተዳድሮች እንኳን ለ1445ኛው የዒድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በመልዕክታቸው የመረዳዳት፣ የመደጋገፍና የተቸገሩ ወገኖች በመርዳትና ካለው ለሌላቸው በማካፈል በዓሉን ማክበር እንደሚገባ አሳስበዋል።

የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች እንኳን ፲ሺህ 445ኛው የዒድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል ባስተላለፈው መልዕክት ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከብር የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት እንዲያከብር አሳስበዋል።

ሕዝበ ሙስሊሙን ጨምሮ መላው የክልሉ ነዋሪ ሰላምን፣ አብሮነትን፣ መተባበርንና ወንድማማችነትን በማጎልበት እንዲሁም በክልሉ እየተከናወኑ የሚገኙ የልማት ተግባራት ድጋፉን እንዲያጠናክር ጠይቋል።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር እንዳሻው ጣሰው ባስተላለፉት መልዕክት፤ የአረፋ በዓል ሲነሳ ስለመንፈሳዊ መደማመጥና ሞራላዊ ስብዕና፣ የበጎነት ስብዕና ስለመላበስ የሚያመላክቱ አስተምህሮቶች አብረው ይነሳሉ ብለዋል።

የአረፋ በዓል በክልሉ ተወላጅ የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ከሃይማኖታዊ በዓልነቱ ባሻገር ተራርቀው የቆዩ ቤተሰቦች በአካል ተገናኝተው የሚጠያየቁበት፣ መንፈሳቸውን የሚያነቃቁበት የእርስ በርስ ግንኙነትን ማደሻ ማህበራዊ እሴትም ጭምር ሆኖ እያገለገለ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ኡሞድ ኡጁሉ በበኩላቸው፤ ሕዝበ ሙስሊሙ የኢድ አል አደሃ (አረፋ) በዓልን ሲያከብር አቅመ ደካሞችን በማገዝ፣ በአንድነትና በወንድማማችነት እንዲከበር ሕዝበ ሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ አንድነቱንና ወንድማማችነቱን ማጠናከር አለበት ብለዋል።

ሕዝበ ሙስሊሙ ታላቁን የአረፋ በዓል ሲያከብር አቅመ ደካሞችን በመጠየቅ፣ የተራቡትን በማብላት፣ የታረዙትን በማልበስ መሆን እንደሚኖርበትም ማመልከታቸውን የክልሉ ኮሙኒኬሽን መረጃ አመላክቷል።

በተመሳሳይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰን በመልዕክታቸው የኢድ አል-አድሀ (አረፋ) በዓል በሃይማኖታዊ ይዘቱም የመታዘዝ፣ የመስዋዕትነት፣ ያለመጠራጠር፣ የእምነት ፅናት ማረጋገጫ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የእስልምና እምነት አስተምህሮ ሰላምን፣ ፍቅርንና መተሳሰብን የሚሰብክ፤ በዜጎች መካከል አብሮነትን፣ አንድነትን፣ ወንድማማችነትን፣ ይቅር ባይነትን የማጎልበት ድርሻው ላቅ ያለ መሆኑ ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ለ፲ ሺህ 445ኛው የዒድ አል-አድሃ (አረፋ) በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከንቲባዋ በመልእክታቸው "እንኳን ለ፲ ሺህ 445ኛው ኢድ አል አድሃ(አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ ብለዋል።

ለመላው ሙስሊም ወገኖቻችን በዓሉ የሰላም፣ የፍቅር፣ የአብሮነት እና የመተሳሰብ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ ሲሉ የመልካም ምኞት መግለጫ መልዕክታቸውን በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው አስተላልፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መልካም የኢድ አል አድሃ (አረፋ ) በዓል!

የኢድ አል አድሃ (አረፋ ) በዓል በእስልምና ዕምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት አንዱ ነው። በዓሉ በእምነቱ አስተምህሮ መሠረት ነብዩ ኢብራሂም የአላህ ትዕዛዝን ለመፈጸም በፍጹም ትህትና እና ታዛዥነት ልጃቸው እስማኤልን ለመስዋዕትነት ያቀረቡበት ነው።

የአረፋ በዓል በቅድስቲቱ ምድር መካ ከሁለት ሚሊዮን በላይ የእምነቱ ተከታዮች ቋንቋ ሳይገድባቸው፣ የቆዳ ቀለም ሳይለያቸው ፣ስፍራና ማንነት ሳያግዳቸው በአንድ አይነት አለባበስ በአንድነት በመሰባሰብ ጥያቄያቸውን ለፈጣሪ የሚያቀርቡበት ነው።

በዓል በሁለት አይነት መልኩ ይከበራል፤ አንደኛው ሃይማኖታዊ መስፈርቶችን ጠብቆ ወደ መካ በመሄድ የሚደረግ የጸሎት ሥነሥርዓት ነው። የሃጂ ተጓዦች ከሚከውኗቸው አበይት ሃይማኖታዊ ተግባራት አንዱና ዋንኛው የአራፋት ተራራን መውጣት ነው። የጤናና የገንዘብ አቅማቸው የፈቀደላቸው ሙስሊሞች ቢያንስ በሕይወት ዘመናቸው አንድ ጊዜ ቅድስቲቱን ምድር መካን በሐጅ ሥርዓት መካፈል ይጠበቅባቸዋል።

ከመካ በስተምሥራቅ 20 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኘውን ቅዱስ ተራራ መመልከትና ሃይማኖታዊ ሥነሥርዓቶችን በዚያው መፈጸም እንደሚገባ የእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮ ያዛል። በዚያም ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስም ቅዱስ ቁርአን እያነበቡ፣ ፈጣሪን እያወደሱና እና የምህረት እጁን እንዲዘረጋ እየለመኑ ይቆያሉ። የሐጅ ጸሎት የሚፈጽም ሰው በዚህ ቀን ከብት የማረድ ግዴታም አለበት።

ሁለተኛው ወደ መካ ለመሄድ ዕድልን ያላገኙ በሀገር ውስጥ የሚገኙ ሙስሊሞች የዒድ ሶላት ሥርዓትን በአንድነት በአደባባይ በደመቀ ሁኔታ ያከብራሉ። ከሶላት በኋላ አቅም ያላቸው ሰዎች በግና ሌሎች እንስሳትን በማረድ አቅም ለሌላቸው ጎረቤቶቻቸው በማካፈል በዓሉን በጋራ ያሳልፋሉ።

በየቤቱ አቅም እንደፈቀደ ምግብ አዘጋጅቶ ከዘመድ ወዳጅ ከጎረቤት ጋር መብላት መጠጣትም በዚህ በዓል የተለመደ ነው። ለኢድ አል አድሃ አንድ ሰው ከሚያርደው ከብት ሲሶውን ብቻ እንዲወስድ፤ ሲሶውን ለችግረኞች፣ የተቀረውን ሲሶ ለጎረቤት እንዲሰጥ የሃይማኖቱ አስተምሮ ያዛል።

የአረፋ በዓል የጋራ የሆኑ ማህበራዊ እሴቶች የሚበለጽጉበት፣ አብሮነት፣ መደጋገፍ፣ መረዳዳትና መተሳሰብ የሚጎለብቱበት ነው፤ በእለቱም እነዚህ ሃይማኖታዊ እሴቶች ጎልተው የሚስተዋሉበት ነው፤ አቅመ ደካሞችንና ረዳት የሌላቸውን በማገዝ የሚከበር ነው። የመረዳዳት በዓል በመሆኑም በእለቱ ያለው ለሌለው ያካፍላል በዚህም የፈጣሪውን ትዕዛዝ ይፈጽማል።

በዓሉ ከዚህም ባለፈ፤ የእምነቱ ተከታዮች ጥፋት ካለባቸው ለጥፋቱ ይቅርታ ጠይቀው ወደ ትክክለኛ መንገድ የሚመጡበት ነው። እርስ በእርሱ በመተዛዘን ለችግሮች መፍትሔ የሚሰጥበት ትልቅ ሃይማኖታዊ መድረክ ነው ። የሐጅ ጉዞ ተንኮልን በመጸየፍ የመተዛዘን፣ የመደጋገፍ ትምህርት የሚቀሰምበት ሃይማኖታዊ ጉዞ ነው።

በዚህ ወቅት የሚስተዋለው ሃይማኖታዊ ተግባራት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው የሚከናወን ተግባር ሊሆን ይገባል። ደካሞችን በሁለንተናዊ መንገድ መርዳት ፣ ለጦም አዳሪዎች የዕለት ጉርሳቸውን ማቅረብ ፣የታረዙትን ማልበስና ወላጅ አልባዎችን መጎብኘት በኢድ አል አድሃ የሚወደድ ተግባር ቢሆንም በሌሎችም ቀናት እነዚህን በጎ ተግባራት አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል ።

የእምነቱ ተከታዮች መረዳዳትን በዓል ሲመጣ ብቻ ሳይሆን የሁልጊዜ ባህል ሊያደርጉት ይገባል፤ ለዚህ ደግሞ የሃይማኖት አባቶች ወደታች ወርደው ምእመኑን ማስተማር ለሁለንተናዊ በጎነት የሚሆን ዝግጁነት እንዲፈጥሩ ማነቃቃት ይጠበቅባቸዋል። ለራሳቸውም ሆነ ለወገኖቻቸው የአብሮነት፣ የመደጋገፍ፣ የመረዳዳት እና የበጎነት ተምሳሌት እንዲሆኑ አበክረው መሥራት ይኖርባቸዋል።

**መልካም የኢድ አል አድሃ (አረፋ ) በዓል!**


**አዲስ ዘመን**

እ ፕ ድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70




## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ለ2016 የዒድ አል አድሃ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላለፉ

**እንኳን ለ2016 የዒድ አል አድሃ በዓል በሰላም አደረሳችሁ**

የኢድ አል አድሃ በዓል የፈተናና የመሥዋዕትነት በዓል ነው። ነቢዩ ኢብራሂም በአላህ ትእዛዝ ልጃቸውን ለመሥዋዕትነት ያዘጋጁበት፤ ጽናታቸው ተፈትኖ ያሸነፉበት በዓል ነው። ለዚህ ጽናታቸውም ከአላህ ዘንድ ምትክ በግ ያገኙበት በዓል ነው።

ከዚህ በዓል የምንማራቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ማንኛውንም ፈተና በጽናት ካለፉት ዋጋው ከፈተናው በላይ መሆኑን እንማርበታለን። ልጅን ያህል ነገር እንዲሰዋ መጠየቅ ከባድ ፈተና ነው። ልጅን ለመሥዋዕትነት ማዘጋጀት ደግሞ ከባድ ጽናት ነው። ከባድ ፈተና ከባድ ቆራጥነት ይፈልጋል። ከባድ ቆራጥነት ከባድ ውሳኔን ይጠይቃል፤ ከባድ ውሳኔም ታላቅ ዋጋን ያስገኛል።

ኢትዮጵያን ታላቅና የበለጸገች ሀገር ለማድረግ ስንነሣ ፈተናው ከባድ እንደሚሆን እናምን ነበር። ሳይፈቱ የተከማቹ ሀገራዊ ችግሮች አሉ። በዘመናችን የተፈጠሩ አሁናዊ ችግሮችም አሉ። እነዚህ ሁለቱን በአንድ ጊዜ መጋፈጥ ይጠይቀን ነበር። ተራራውን መጋፈጥ ሳይሆን ተራራውን ማንሣት ይጠይቀን ነበር። ይሄንን ፈተና ለመጋፈጥ ከባባድ ውሳኔዎችን መወሰን ይገባን ነበር። እንደ ልጅ የምንወዳቸውን ሰዎች፣ ነገሮች፣ ቡድኖች፣ ወዳጆችና አካሄዶች ለመሠዋት መወሰን ነበረብን። መወሰን ብቻ ሳይሆን ማድረግም ነበረብን።

ነቢዩ ኢብራሂም ልጃቸው ኢስማኤልን ሳይሆን በምትኩ ከአላህ የተሰጣቸውን በግ ሠውተዋል። የእኛ ፈተና ከዚህም የባሰ ነበር። ሀገራችን ባከማቸቻቸው ዕዳዎችና ስብራቶች የተነሣ፣ ያለን አማራጭ የራሳችንን ነገር መሠዋት ብቻ ነበር። ሀገራችንን ለማዳን፣ የሕዝባችንን ዘላቂ ጥቅሞች ለማስከበር እና ከዛሬው የተሻለ ነገን ለመፍጠር ስንል፣ ብዙ ነገሮችን ሠውተናል።

ችግሮቻችን ቀስ ብለን እንድንሄድ አይፈቅዱልንም። በጥንቃቄ እንድንሮጥ እንጂ። የልማት ጥያቄዎቻችንን ለመመለስ እንደ ሕዝብ ሁላችንም የምንወዳቸውን ነገሮች ሠውተናል። ከምንወደው አካባቢ ወደ ሌላ ሄደናል።

ትዝታዎቻችንን ሠውተናል። የባንዳውን ጩኸት ችለናል፤ ሀገርን ለመለወጥ ስንል ቤቶቻችንና ሕንፃዎቻችን እንዲፈርሱ ፈቅደናል። የመብራትና የውሃ መጥፋትን ታግሰናል፤ የመንገድ መዘጋትንና የአካባቢ መፈራረስን ተቀብለናል። ያለ መሥዋዕትነት የሚያድግ ሕዝብ፣ ያለ መሥዋዕትነት የሚበለጽግ ሀገር የለም። የኮሪደር ልማቱን በዚህ መልኩ በመሥዋዕትነት ነው የሠራነው። ፍሬው ግን እጅግ ጣፋጭ መሆኑን አይተናል።

ሰላማችንን ለማስፈን በዚሁ መንገድ ነው መቀጠል ያለብን። ነፍጥን መጣል፣ ከጫካ መውጣትና የራስን ዋሻ ትቶ ወደ መስኩ መውጣትን ይፈልጋል። የራስን ኢጎ መሠዋትን ይጠይቃል። ምኞትንና ፍላጎትን መተውን ይፈልጋል። ከመቀበል በላይ መስጠትን ይሻል። እንደ ኢብራሂም በጣም የምንሳሳለትን ነገር ለመሠዋት መቁረጥ ይፈልጋል። ሁላችንም ለመሥዋዕትነት ከተዘጋጀን የማይሳካ የሰላም መንገድ የለም። እንደ ልጅ ያሳደግናቸው ብዙ ልማዶች፣ ጠባዮች፣ አመለካከቶች፣ ርእዮተ ዓለሞችና አካሄዶች አሉን። እነርሱን ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም ስንል ለመሠዋት ዝግጁ ከሆንን፣ ውጤቱ ከሰላም በላይ ነው።

ምክክር የሚሳካው የተሻለ ሐሳብና የላቀ ዕውቀት በማዋጣት ብቻ አይደለም። የተሻለ ሐሳብና የላቀ ዕውቀት ስላለን ብቻ የሠመረ ውጤት አናገኝም። ሌላ ወሳኝ ነገር ይፈልጋል። እርሱም መሥዋዕትነት ነው። የራስን ፍላጎት ለመሠዋት መቻል አለብን። ለትልቅ ግብ ሲባል ይቅርብኝ ማለት አለብን። ከእኔ የተሻለ ሐሳብና ልምድ፣ ዕውቀትና ጥበብ ሊኖር ይችላል ብለን ማመንና መቀበል አለብን። ለተሻለው ሐሳብ መገዛት አለብን። ልክ ልኩን ከመንገር፤ ነጥብ ከማስቆጠር፤ ጀግና ጀግና ከመጫወት የወጣ ትጉት ሰብእና መያዝ አለብን። ይሄ ሁሉ መሥዋዕትነትን ይጠይቃል።

እንደ ነቢዩ ኢብራሂም ያሳደግናቸውን ብቻ ሳይሆን አብረውን ያደጉትን ብዙ ጠባዮች ለመሠዋት መዘጋጀትን ይጠይቃል። መሥዋዕትነት የሚከፍሉ ዜጎች በበዙ ቁጥር፣ ምክክር የላቀ ውጤት ያስገኛል።

የኮሪደር ልማታችን በየከተሞቻችን እንዲስፋፋ፣ ሰላማችን የጸና እና የማይደፈርስ እንዲሆን፤ ሀገራዊ ምክክሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ተካሂዶ እንዲሳካ - ያሳደግናቸውንና ያደጉብንን አንዳንድ ነገሮች መሥዋዕት ለማድረግ እንዘጋጅ። ሐሳቦቻችን ትጥቅ ይፍቱ። ከመተኮሻ ወደ ማረሻ እንመለስ። ከጠመንጃ ወደ ማጨጃ እንዛወር። ከዲሞትፈር ወደ ምክክር እንምጣ። ከብሔር ግጭት ወደ ሐሳብ ፍጭት እንሻገር። የምንወደውን፣ የምንፈልገውንና ያሳደግነውን እንኳን ቢሆን - ለሀገር ስንል ለመሠዋት እንዘጋጅ።

መልካም በዓል ይሁን።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**ሰኔ 8 ቀን 2016 ዓ.ም**

# አውሮፕላኖቹ ከኢትዮጵያ አልፎ ለጎረቤት ሀገራት አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ ናቸው

**መስከረም ሰይፋ**

አዲስ አበባ፡- የአሰሳና የርጭት አውሮፕላኖቹ ከኢትዮጵያ አልፎ ለጎረቤት ሀገራት አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ መሆናቸውን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር በቅርቡ ተገዝተው ወደ ሀገር የገቡት 5 የአሰሳና የርጭት አውሮፕላኖች የግብርና ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች፣ የናሽናል ኤር ዌይስ አመራሮች እንዲሁም የክልል የግብርና ቢሮ ኃላፊዎች በተገኙበት የሥራ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር በትናንትናው እለት ተካሂዷል።

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ግብርናውን ለማዘመንና ምርትን ለማሳደግ በትኩረት እየሠራች ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የስንዴና ሌሎች ሰብሎች ላይ በአንበጣ፣በግሪሳ ወፍና በተምች እየተጠቃች ትገኛለች። እነዚህን ተባዮች ሙሉ ለሙሉ ማስቀረት የማይቻል ቢሆንም የመቀነስና ለመከላከል የሚያስችል አቅም መፍጠር አስፈላጊ ነዉ።

የርጭትና የአሰሳ አውሮፕላኖችን እየተከራዩ ለመከላከል ከመሞከር ይልቅ የራስ አቅም ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በ850 ሚሊዮን ብር ወጪ አምስት አውሮፕላኖች መግዛታቸውን ገልጸዋል።

ይህም ሀገሪቷ የሰበል በሽታዎችንና ተባዮችን ለመከላከል የምታወጣውን ወጪ እንደሚቀንስ ገልጸው፤ ለአብነትም ከሦስት ዓመት በፊት በተከሰተ የአንበጣ መንጋ ለመከላከል ከ13 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ መውጣቱንና ይህም ከአውሮፕላኖቹ የግዢ ዋጋ ጋር የሚነጻጸር አለመሆኑን አንስተዋል።

ሚኒስትሩ አውሮፕላኖቹ የግሪሳ ወፍን ፣ የበረሀ አንበጣ መንጋና ተምችን ለመከላከል ታስቦ የተገዙ የነበረ ቢሆንም ጸረ አረም የመርጨትና እሳት የማጥፋት አገልግሎት ጭምር መስጠት የሚችሉ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ ሌሎች የጎረቤት ሀገራት የአውሮፕላኖቹን አገልግሎት ለማግኘት የጠየቁ ሲሆን፤ ይህም ተጨማሪ የውጪ ምንዛሬ ማግኛ መሆኑን ገልጸዋል።

በትናንትናው እለትም የኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽንና የኦሮሚያ ምርጥ ዘር ድርጅት የአውሮፕላኖቹን አገልግሎት ለማግኘት ከግብርና ሚኒስቴር ጋር ተፈራርመዋል።



# “የዒድ አል አድሃ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኢትዮጵያን ታላቅና የበለጸገች ሀገር ለማድረግ ስንነሣ ፈተናው ከባድ እንደሚሆን እናምን ነበር። ሳይፈቱ የተከማቹ ሀገራዊ ችግሮች አሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዘመናችን የተፈጠሩ አሁናዊ ችግሮችም አሉ። እነዚህ ሁለቱን በአንድ ጊዜ መጋፈጥ ይጠይቀን ነበር። ይሄንን ፈተና ለመጋፈጥ ከባባድ ውሳኔዎችን መወሰን ይገባን ነበር። እንደ ልጅ የምንወዳቸውን ሰዎች፣ ነገሮች፣ ቡድኖች፣ ወዳጆችና አካሄዶች ለመሠዋት መወሰን ነበረብን። መወሰን ብቻ ሳይሆን ማድረግም ነበረብን ብለዋል።

ነቢዩ ኢብራሂም ልጃቸው ኢስማኤልን ሳይሆን በምትኩ ከአላህ የተሰጣቸውን በግ ሠዉተዋል። የእኛ ፈተና ከዚህም የባሰ ነበር። ሀገራችን ባከማቸቻቸው ዕዳዎችና ስብራቶች የተነሣ፣ ያለን አማራጭ የራሳችንን ነገር መሠዋት ብቻ እንደነበር ገልጸው፤ ሀገራችንን ለማዳን፣ የሕዝባችንን ዘላቂ ጥቅሞች ለማስከበር እና ከዛሬው የተሻለ ነገን ለመፍጠር ስንል፣ ብዙ ነገሮችን ሠዉተናል ነው ያሉት።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ገለጻ፤ችግሮቻችን ቀስ ብለን እንድንሄድ አይፈቅዱልንም። በጥንቃቄ እንድንሮጥ እንጂ። የልማት ጥያቄዎቻችንን ለመመለስ እንደ ሕዝብ ሁላችንም የምንወዳቸውን ነገሮች ሠዉተናል። ከምንወደው አካባቢ ወደ ሌላ ሄደናል። ትዝታዎቻችንን ሠዉተናል። የባንዳውን ጨኸት ችለናል።ያለ መሥዋዕትነት የሚያድግ ሕዝብ፣ ያለ መሥዋዕትነት የሚበለጽግ ሀገር የለም።

የኮሪደር ልማቱን በዚህ መልኩ በመሥዋዕትነት ነው የሠራነው። ፍሬው ግን እጅግ ጣፋጭ መሆኑን አይተናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤

ሰላማችንን ለማስፈን በዚሁ መንገድ ነው መቀጠል ያለብን። ነፍጥን መጣል፤ ከጫካ መውጣትና የራስን ዋሻ ትቶ ወደ መስኩ መውጣትን ይፈልጋል ብለዋል።

እንደ ልጅ ያሳደግናቸው ብዙ ልማዶች፣ ጠባዮች፣ አመለካከቶች፣ ርእዮተ ዓለሞችና አካሄዶች አሉን። እነርሱን ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም ስንል ለመሠዋት ዝግጁ ከሆንን፣ ውጤቱ ከሰላም በላይ መሆኑን ገልጸው፤

ምክክር የሚሳካው የተሻለ ሃሳብና የላቀ ዕውቀት በማዋጣት ብቻ አይደለም። የተሻለ ሃሳብና የላቀ ዕውቀት ስላለን ብቻ የሠመረ ውጤት አናገኝም። ሌላ ወሳኝ ነገር ይፈልጋል። እርሱም መሥዋዕትነት መሆኑን አመልክተዋል።

ልክ ልኩን ከመንገር፣ ነጥብ ከማስቆጠር፣ ጀግና ጀግና ከመጫወት የወጣ ትጉት ሰብእና መያዝ አለብን። ይሄ ሁሉ መሥዋዕትነትን ይጠይቃል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር) እንደ ነቢዩ ኢብራሂም ያሳደግናቸውን ብቻ ሳይሆን አብረውን ያደጉትን ብዙ ጠባዮች ለመሠዋት መዘጋጀትን ይጠይቃል። መሥዋዕትነት የሚከፍሉ ዜጎች በበዙ ቁጥር፣ ምክክር የላቀ ውጤት ያስገኛል ነው ያሉት።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) የኮሪደር ልማታችን በየከተሞቻችን እንዲስፋፋ፤ ሰላማችን የጸና እና የማይደፈርስ እንዲሆን፤ ሀገራዊ ምክክሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ተካሂዶ እንዲሳካ ያሳደግናቸውንና ያደጉብንን አንዳንድ ነገሮች መሥዋዕት ለማድረግ እንዘጋጅ ብለዋል።

ሃሳቦቻችን ትጥቅ ይፍቱ። ከመተኮሻ ወደ ማረሻ እንመለስ። ከጠመንጃ ወደ ማጨጃ እንዛወር። ከዲሞትፈር ወደ ምክክር እንምጣ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከብሔር ግጭት ወደ ሃሳብ ፍጭት እንሻገር። የምንወደውን፣ የምንፈልገውንና ያሳደግነውን እንኳን ቢሆን - ለሀገር ስንል ለመሠዋት እንዘጋጅ ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# በአረፋ በዓል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያ እስልምና ጠቅላይ ምክር ቤት የፕሬዚዳንቱ አማካሪና የውጭ ግንኙነት ኃላፊና የታሪክ ተመራማሪ አደም ካሚል ገለጹ።

አደም ካሚል የ1445ኛው የዒድ አልአደሃ(አረፋ) በዓልን አስመልክተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአረፋ በዓል የጋራ የሆኑ ማህበራዊ እሴቶች የሚበለጽጉበት፣ አብሮነት፣ መደጋገፍ፣ መረዳዳትና መተሳሰብ የሚጎለብቱበት በመሆኑ ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከበር አቅመ ደካሞችንና ረዳት የሌላቸውን በማገዝ ሊሆን ይገባል።

እንደ አደም ካሚል ገለጻ፤ የዒድ አልአድሃ አረፋ በዓል በእምነቱ አስተምህሮ መሠረት ነብዩ ኢብራሂም የአሏህ ትዕዛዝን ለመፈጸም በፍጹም ትህትና እና ታዛዥነት ልጃቸው እስማኤልን ለመሥዋዕትነት ያቀረቡበት በዓል ነው። በዚህም በዓሉ ሲከበር ከራስ በላይ ለሌሎች በማሰብ ለመሥዋዕትነት ከቀረበው ለተቸገሩ ወገኖች ማካፈል ግዴታ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአረፋ በዓል እርድ አርዶ ለጎረቤት፣ ለዘመድ፣ ለችግረኞች፣ በሰፊው የምናካፍልበት በዓል መሆን እንዳለበት የጠቀሱት የታሪክ ተመራማሪው፤ ይህ በነቢዩ ኢብራሂም የተሰጠው ትምህርት አንድ ሰው እርድ አርዶ አንድ ሦስተኛውን ለራሱ፣ አንድ ሦስተኛውን ለችግረኞች፣ አንድ ሦስተኛውን ለጎረቤት ይሰጣል። ይህም አብሮ መብላትና መካፈልን ያመጣል ብለዋል።

የመሥዋዕትነትና የመታዘዝ በዓል የሆነው የአረፋ በዓል የሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ ልዩ ትርጉም እንዳለው ገልጸው፤ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረው የአረፋ በዓል ትልቁ የሐጅ በዓል የሚከበርበት ቦታ በመሆኑ በዓሉ የሰው ልጆችን እኩልነት፣ የመተዛዘን፣ የመከባበር፣ ሥርዓትን የሚገልጽ መሆኑን ተናግረዋል።

አረፋ ማለት አደምና ሐዋ የተገናኙበት ቦታ ነው ያሉት አደም (ረዳት ፕሮፌሰር)፣ የአረፋ በዓል በአንድ ቦታ በአንድ አለባበስ ከሁለት ሚሊዮን በላይ የእምነቱ ተከታዮች ቋንቋ ሳይገድባቸው፣ ጥቁሩ፣ ነጩ፣ ሁሉም ስፍራና ማንነት ሳያጥረው በአንድነት በመሰባሰብ ጥያቄያቸውን ለፈጣሪ የሚያቀርቡበት ነው ብለዋል።

ፈጣሪም ምህረቴን ሰጥቻችኋለሁ ብሎ የሚያውጅበት፣ በሐጁ ያልተጋበዙና ዕድሉን ያላገኙ በየሀገራቱ የሚኖሩ በጾምና ጠዋት ላይ አደባባይ ወጥተው የዒድ ሶላት ሥርዓትን እንደሚያከናውኑ ረዳት ፕሮፌሰር አደም አስረድተዋል።

የአረፋ በዓል የእምነቱ ተከታዮች ጥፋት ካለባቸው ለጥፋቱ ይቅርታ ጠይቀው ወደ ትክክለኛ መንገድ የሚመጡበት ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ እርስ በእርሱ በመተዛዘን ለችግሮች መፍትሔ የሚሰጥበት ትልቅ ሃይማኖታዊ መድረክ እንደሆነም ጠቁመዋል። የሐጅ ጉዞ ተንኮልን በመጸየፍ የመተዛዘን፣ የመደጋገፍ ትምህርት የሚቀሰምበት ሃይማኖታዊ ጉዞ እንደሆነም አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶችን ተቀብላ ያስተናገደች ሀገር መሆኗን ጠቅሰው፤ ሁሉም ዜጋ በእኩልነትና በሰላም መኖር እንዲችል መሥራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። ሰላምና አንድነቷ አርማዋ ለሆነች ሀገር በአብሮነትና በመቻቻል መኖር ወሳኝ ነው ብለዋል።

የአረፋ በዓል መገለጫ የሆነው የመደጋገፍና የመረዳዳት ባህል እንዲጎለብት የሃይማኖት አባቶች ወደ ታች ወርደው ተከታዮቻቸውን ሊያስተምሩ እንደሚገባ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ገልጸዋል።

መረዳዳት በዓል ሲመጣ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜም ባህል ልናደርገው ያስፈልጋል ያሉት የታሪክ ተመራማሪው፤ ሰላም፣ መረጋጋትና ልማት እንዲመጣ የሃይማኖት አባቶች ትልቅ ሚና አላቸው ብለዋል። ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች መልካም የአረፋ በዓል እንዲሆን ተመኝተዋል።

# ሕዝበ ሙስሊሙ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሼህ ሱልጣን አማን ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ ኢትዮጵያ የተለያየ እምነት ተከታይ ለበርካታ ዘመናት ተዋዶና ተከባብሮ የኖረባት ሀገር እንደመሆኗ ምዕመኑ ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር አንድነቱንና ወንድማማችነቱን ይበልጥ በማጠናከር በዓሉን ማሳለፍ እንዳለበት አስገንዝበዋል።

በመካሄድ ላይ በሚገኘው ሀገራዊ ምክክር በኢትዮጵያ ታሪክ የነበሩ ክፍተቶችን በመሙላት ለሕዝበ ሙስሊሙ ሁለንተናዊ መብትና ጥቅም መከበር መልካም አጋጣሚ የሚያስገኝ መሆኑን ገልጸው፤ ሕዝበ ሙስሊሙ ተሳትፎውን በማጠናከር ኃላፊነቱን እንዲወጣም ሼህ ሱልጣን አማን ጥሪ አቅርበዋል።

ኢማሞችና ኡስታዞች ባሉበት ሁሉ ስለ ሰላም መምከር እንዳለባቸውም አሳስበው፤ በዓሉ የሰላም፣ የደስታና የአብሮነት እንዲሆን ተመኝተዋል።

የምክር ቤቱ የሚዲያና ኮሚኒኬሽን ኃላፊ ኡስታዝ ሀሰን አሊ በበኩላቸው፤ ሙስሊሞች በደስታ፣ በመተጋገዝና በመረዳዳት ከሚያሳልፏቸው በዓላት መካከል ትልቁ ዒድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል መሆኑን ገልጸው፤ በዓሉን ስናከብር ማካፈልን፣ አንዱ ለአንዱ መድረስን የምንተገብርበትና ፍፁም ሰብዓዊ የሆነ ተግባራት የሚከናወኑበት የአብሮነት ማሳያ በዓል ነው ብለዋል።

ኡስታዝ ሀሰን በመግለጫቸው፤ ከሶላት በኋላ የሚታረድ ዕርድ (ኡዱሁያ) ከጎረቤቱ ጋር በመሆን ለወላጅ አልባ ሕፃናት፣ ለአዛውንቶችና ለተቸገሩ ዜጎች ያላቸውን በማካፈል እንዲያከብሩ አመላክተዋል።

የዘንድሮ ዒድ ሲከበር ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ሰዎች ሊረዳዱና ሊተጋገዙ የሚገባቸው ወቅት ነው ያሉት ኡስታዝ ሀሰን፤ ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከብር በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖቻችንን በማሰብ፣ በማገዝና በዓሉን ተደስተው እንዲያሳልፉ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

በዓሉን በሰላም ለማክበር የቅድመ ዝግጅት መደረጉን ገልጸው፤ የከተማው ሙስሊም ኅብረተሰብ በዓሉን በሰላም እንዲያሳልፍ ከጸጥታ አካላት ጋር የተለመደ ትብብር እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

የኢድ ሶላት ሥነ ሥርዓት ዛሬ ሁለት ሰዓት በአዲስ አበባ ስቴዲየም እንደሚከናወንም ተገልጿል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ባላየ ባልሰማ እያለፍነው ያለ ነጩ ዝሆን

በዚህ ዕለተ ሰንበት መጋቢ ሀዲስ አለማየሁ በebs ቡና ሰዓት ላይ ቀርበው፤ ከማር ከወለላ በሚጣፍጠው ወጋቸው ስለ እርቅ አስፈላጊነት ሲሰብኩ አደመጥኩ። እሳቸው በአውደ ምህረቱ ብቻ ሳይሆን በሄዱበትና በደረሱበት ቢያወጉ፣ ንግግር ቢያደርጉ፤ የዕምነት አጥርን የተሻገረ ስብከት ነው የሚያካሂዱት የሚል መረዳት አለኝ። በዚህ የebs"ስብከታቸው"ሰው መጀመሪያ ከፈጣሪው በማስከተል ከራሱ ከዚያ ከተፈጥሮ በመቀጠል ከማህበረሰቡ ጋር መታረቅ አለበት ሲሉ በየቤታችን ያለውን ግን ልብ ያላልነው፤ ልብ ብንለውም ቦታ ያልሰጠነውን ነጭ ዝሆን አስታወሱኝ።

ሕዝብ እንደ ሕዝብ አልተጣላም፣ ማን ከማን ጋር ነው የሚታረቀው፤ የተጣላው ያው ተማርሁ ፊደል ቆጠርሁ የሚለው እንጂ ሕዝብማ አብሮ እየተኗኗረ ነው። ነጮች white elephant in the room እንዲሉ። አወዛጋቢ ወይም አነጋጋሪ ነገር እንዳለ ልብ እያወቀ የውሾን ነገር ያነሳ ውሾ ይሁን ተብሎ ሲተው ነጮች በቤት ውስጥ ያለ ነጭ ዝሆን ይላሉ። በየቤታችን፣ በየቀዬው፣ በየጋራ፣ ሸንተረሩ፣ በየአውራ መንገዱ፣ በየአዳራሹ፣ በየቢሮው፣ በየስራ ቦታው፣ ወዘተረፈ በአካል ግዘፍ ነስቶ ባናየውም በሀሰተኛ ትርክት ምስ ተወልዶ የጎለመሰ ጥላቻ የሚባል አባት ነጭ ዝሆን አለ። መጠራጠር፣ መለያየት፣ መጠፋፋት፣ ግጭት፣ ማገት ውድመት፣ ጦርነት፣ ቀውስ፣ ወዘተረፈ የሚባሉ ዲቃላዎች አሉት።

ከግዝፈቱና ከንጣቱ አንጻር ባላየና ባልሰማ ሊያልፉት የማይችል። በአቋራጭና በተለዋጭ መንገድ ወይም ዲቶር ሊያልፉት ቢሞክሩ፤ በማለባበስ፣ ጭምብል በማጥለቅ፣ በማድበስበስ፣ በመሸፋፈን፣ በመቀባባትና በመኳኳል ሊያልፉት ቢሞክሩ ቀድሞ የሚገኝ አባት ነጭ ዝሆን። የሀገራዊ ምክክሩ አንዱ ምሰሶ ይሄን አባት ነጭ ዝሆን እንዳይመለስ አድርጎ ማሰናበት ነው። ይህ እንዲሆን ደግሞ ሀገራዊ ምክክሩን በማዕቀፍ ከአዳራሽ ባሻገር የማየት ድፍረት ይጠይቃል።

ከዚህ ቀደም ደጋግሜ እንደምለው ከአዳራሽ ባሻገር በማዕቀፍ ማየት ይሻል። በአዳራሽ ጀምረው በአዳራሽ የማይቋጩት። ማዕቀፉ ግልጽ ነው። ከፈጣሪ፣ ከራስ፣ ከተፈጥሮና ከጎረቤት ጋር መምከር፣ መግባባትና መቀባበል የሚጠይቅ ማዕቀፍ ወይም ፓኬጅ ነው። ከራስና ከፈጣሪ ጋር የሚደረግ እርቅ ቆም ብሎ ራስን በመመርመርና የመጡበትን መንገድ በመገምገም ከራስም ሆነ ከፈጣሪ ጋር ጸብና ቅራኔ ካለ እርቅ ለማውረድ የሚወሰንበት ሒደት ነው። ከራሱና ከፈጣሪው ጋር ሰላም የሌለው ከሌሎች ጋር ሰላም ሊኖረው አይችልምና የሀገራዊ ምክክርም ሆነ የእርቅም አካል ሊሆን አይችልም።

ከራስና ከፈጣሪ ጋር እርቅ ማውረድ ለሀገራዊ ምክክርና እርቅ መሠረት ነው። ከፈጣሪም ሆነ ከራስ ጋር የሚደረግ ሰላም ግለሰባዊ ውሳኔ ቢሆንም የሀይማኖት ተቋማትና ብዙኃን መገናኛዎች የበኩላቸውን እገዛ ሊያደርጉ ይገባል። ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ ከተፈጥሮ ጋር በአረንጓዴ አሻራ አሸማጋይነት እያታረቅን ነው። ባለፉት አራት ዓመታት ከ25 ቢሊየን በላይ ችግኞችን የተከልን ሲሆን ከዘንድሮው ጋር 32 ቢሊየን እንደርሳለን። ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ 50 ቢሊየን እንደርሳለን። በዚህ ከእናት ምድርና ተፈጥሮ ጋር ሰላም እያወረድን ነው ።

በነገራችን ላይ ሀገራዊ ምክክሩ ከማዕቀፉ አንዱን ካጎደለ ሙሉኡ አይሆንም። ይህ ማለት መሉ በኩሌ እንዲሆን ይጠበቃል ማለት አይደለም። የጎደለውን ተብድሮም ሆነ ተለቅቶ የመሙላት ኃላፊነትና ቁርጠኝነት ይጠይቃል። በዚህ ሀገራዊ ምክክር ሒደት ጎን ለጎን ሊሟሉ ከሚገባቸው አላባውያን አንዱና ዋነኛው ኢኮኖሚው ነው። ከእሱ ጋር ቁጭ ብሎ በጥሞና መነጋገርና መመካከር ይጠይቃል። የሀገራዊ ምክክሩ አካል ሊሆን ይገባል። ሆኖም የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሀገራዊ ምክክር ማዕቀፎችን ሁሉ ይሸከም። ይወጣው አይባልም።

በተለይ መንግስት፣ ባለድርሻ አካላትና መላ ሕዝቡ በመቀናጀትና በመናበብ የኑሮ ውድነቱን፣ የዋጋ ግሽበቱን፣ አጉራ ዘለል የግብይት ስርዓቱን፣ ስራ አጥነቱን፣ ኢፍትሐዊ የሀብት ክፍፍሉን፣ የተፈጥሮ ሀብት ብሔርተኝነቱን፣ ወዘተረፈ አደብ በማስገዛት የሀገራዊ ምክክሩ ቀልብ እንዳይወሰድ ማገዝ አለባቸው። በሀገሪቱ የሚስተዋለው የጸጥታ ችግርም ሀገራዊ ምክክሩ ላይ ተጽዕኖ እንዳሳያድር በማያዳግም አግባብ ከወዲሁ መቀረፍ አለበት። የብሔር ጽንፈኝነትም ለሀገራዊ ምክክሩ እንቅፋት እንዳይሆን በጥበብና በማስተዋል ሊያዝ ይገባል። የዛሬ መጣጥፌ መነሻና መዳረሻ ወደ ሆነውና ከሀገራዊ ምክክር ማዕቀፎች አንዱ ወደሆነው "ነገረ ኢኮኖሚ" ልመለስ። ኢኮኖሚያዊ ነባራዊ ሁኔታው ከሀገራዊው ምክክሩ ጋር ያለውን መስተጋብር ላነሳሳ።

ኢኮኖሚያዊ ሁናቴ በተለይ በድህረ ግጭትና ቀውስ ወቅት በሀገራዊ ምክክር ሂደት ውስጥ የማይተካ ሚና አለው። ሀገራዊ ምክክር በቀውስና በግጭት ወቅት በማህበረሰቦች መካከል የተፈጠሩ ቁስሎችና ልዩነቶች እንዲታከሙ በማድረግ መተማመን መፍጠር እንዲሁም ለግጭትና ለቀውስ የዳረጉ ቁርሾዎችን በዘላቂነት የመፍታት ሂደት ነው። በዚህ ወሳኝ ሂደት ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ሁናቴው የሀገራዊ ምክክሩን ስኬትም ሆነ ውድቀት የመወሰን አቅም አለው። በማህበረሰቦች መካከል የተፈጠረ የኢኮኖሚ ኢፍትሐዊ ተጠቃሚነት ውጥረትንና ቅሬታን በመጎንቆል ወደ ለየለት ግጭት ሊያመራ ይችላል። የማህበረሰቦችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ፍትሐዊ በማድረግ ግጭቶችን አስቀድሞ ማምከን ይገባል። የሀገራዊ ምክክር ጥረቶች ሁሉም ዜጎች ፍትሐዊና እኩል የኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ዕድል እንዲፈጠርላቸው ማለትም ለሀብት፣ ለትምህርት፣ ለስራ ዕድል፣ ወዘተረፈ እኩል ተደራሽነት እንዲኖራቸው ያበረታታሉ። ፍትሐዊነትን ይመክራሉ።

ሌላው በተለይ በድህረ ግጭትና ቀውስ መልሶ ግንባታና ልማት በስፋት ካልተካሄደ ሀገራዊ ምክክሩንም ሆነ ብሔራዊ እርቁን የተሟላ አያደርገውም ። መሠረተ ልማቶችን መልሶ መገንባት፤ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ማሟላት፤ በግጭቱ የተቀዛቀዘውን ኢኮኖሚ ማነቃቃት እና ነገሮችን ቀድመው ወደነበሩበት መመለስ ለሀገራዊ ምክክሩ መደላድል ይፈጥራል። የመብራት የቴሌኮም የባንክ በቅርብ ደግሞ የአክሱም አውሮፕላን ተጠናቆ በረራ ጀምሯል። ስራ አቁመው የነበሩ ፋብሪካዎች ወደ ስራ ተመልሰዋል።

ከዚህ አኳያ መንግስት ከፊቱ ብዙ ስራ ይጠብቀዋል። በግብርናው፣ በኢንዱስትሪውና በንግድ እንቅስቃሴው በሰፊው መዋዕለ ነዋይ ማፍሰስ የስራ ዕድልና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ስለሚያመጣ መረጋጋት ይፈጥራል። ቅሬታን ያለዝባል። አንዳንድ የዘርፉ ልሒቃን የሽግግር ፍትሕ ስርዓት፣ የእርቅ አፈላላጊና የካሳ ስርዓቱን የሀገራዊ ምክክር ሒደቱ አካል አድርገው ያዩታል። የተጎዱትን መካስ፣ ሀብት የማፍራት መብትን እንደገና ማረጋገጥ፣ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ወይም ማህበረሰቦች የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ቁስል እንዲጠግግና ምክክሩ ወደፊት እንዲራመድ ያግዛል።

ቀደም ሲል በተፈጠሩ ግጭቶችና ቀውሶች የተቃቃሩ ማህበረሰቦችን ለማቀራረብና ይቅር ለማባባል ኢኮኖሚያዊ ውህደትና ትብብር የላቀ አስተዋጾ አለው ይላሉ እነዚሁ የዘርፉ ምሁራን። ሌላው ኢኮኖሚያዊ

**በዚህ ወሳኝ ሂደት ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ሁናቴው የሀገራዊ ምክክሩን ስኬትም ሆነ ውድቀት የመወሰን አቅም አለው። በማህበረሰቦች መካከል የተፈጠረ የኢኮኖሚ ኢፍትሐዊ ተጠቃሚነት ውጥረትንና ቅሬታን በመጎንቆል ወደ ለየለት ግጭት ሲያመራ ይችላል**

መረጋጋትና መልካም አስተዳደርም ለሀገራዊ ምክክሩ ጥሩ መደላድል ስለሚፈጥር ከወዲሁ ልዩ ትኩረት ይሻል። ይሁንና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ብቻ የተዋጣለት ሀገራዊ ምክክርና እርቅ ያሳካሉ ማለት አይደለም። የማህበራዊና የባህላዊ፣ የስነ ልቦናና የፖለቲካ ጉዳዮችም የላቀ ድርሻ እንዳላቸው በቅጡ ሊጤኑ ይገባል።

ኢኮኖሚው ችግሮቻችን የመፍቻ ዋና ቁልፍ (ማስተርኪይ) ነው። አሁን ከገባንበት ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቅርቃር የመውጫ የማሪያም መንገዳችን ነው። ሀገርም ሕዝብም ሆኖ ለመዳን ፍቱን መድሀኒታችን ነው። የኑሮ ውድነት፣ የዋጋ ግሽበት፣ ስራ አጥነት፣ ድህነት፣ ችጋር፣ ቸነፈር፣ ጠኔ፣ ርሀብ፣ እርዛት ብሔር ወይም ሀይማኖት የላቸውም። አማራም፣ ትግራዋይም፣ ኦሮሞም፣ ሶማሌም፣ አፋርም፣ ወዘተረፈ አይደሉም። ኦርቶዶክስ፣ እስላም፣ ክርስቲያን፣ ካቶሊክ፣ ዋቄ ፈናም አይደሉም። ያለልዩነት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ችግሮች ናቸው። ቢቀረፉ ሁሉንም ያለልዩነት እልል የሚያሰኙ፤ ባይቀረፉ በአንድነት ጥያቄ የሚሆኑ ናቸው።

በዚህ ሰዓት ኢትዮጵያውያንን በአሉታም ሆነ በአንድነት የሚያቆማቸው በኢኮኖሚው ላይ በሚመዘገው ስኬት ወይም ውድቀት ነው። ሰንደቅ ዓላማ፣ ሀገር፣ ብሔራዊ ጀግና፣ ታሪክ፣ ወዘተረፈ በ2ኛ ደረጃ የሚገኙ ናቸው። የዚህ ለውጥ አስኳል ኢኮኖሚው ነው። ሌሎች እሱን ተከትለውና በእሱ ዙሪያ የሚመሠረቱ ናቸው። ሀቀኛና እውነተኛ ብሔራዊ መግባባትና እርቅ ላይ ለመድረስም ኢኮኖሚው ወሳኝ ሚና አለው። ቻይናንና ቬትናምን ይዞ የተነሳው፤ ዜጎቿን ያግባባው፤ ሳይመካከሩ ያስታረቀው፤ ይቅር ያባባለው፤ አንድነታቸውን በጹኑ መሠረት ላይ ያቆመው፤ በኩራት ቀና ብለው እንዲራመዱ፤ ወዘተረፈ ያደረገው ኢኮኖሚው ነው። እንጂ ከቻይና የእርስ በርስ ጦርነቱና ከባህል አብዮቱ በላይ ደም ያቃባ ግጭት የለም። በኢኮኖሚው ያስመዘገቡት ተአምራዊ ዕድገት ጠባሳው እንዲሽር አድርጓል።

ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ማለትም የኑሮ ውድነቱ ፣ ስራ አጥነቱ ፣ ግሽበቱ ፣ ከትልቅ መንግስትነት ወደ ትንሽ መንግስትነት ማለትም መንግስት በሒደት ኢኮኖሚውን ለገበያውና ለዜጋው ትቶ እሱ ድንበር፣ የሕግ የበላይነት፣ መልካም አስተዳደር፣ ወዘተረፈ ላይ ሲያተኩር ዜጋው መሰረታዊ ፍላጎቱን አሟልቶ በሂደት ጥሪት፣ ሀብት ሲያፈራ፣ ተስፋ ሲሰንቅ ወዘተረፈ በሂደት ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ ቀውሶችን ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት ያቀለዋል። ተስፋ ከሰነቀ፣ ስራ ካለው፣ በኑሮ ውድነትና በዋጋ ግሽበት ካልተማረረ፣ በየሰዓቱ በሚያሻቅብ የሸቀጥ ዋጋ ካልተራቆተ፣ የትርፍ ህዳግ ከተቀመጠለት እንደ አሸዋ ከበዛ ቀማኛ ደላላ ከተላቀቀ፣ ስለሚበላውም ሆነ ለልጆቹ ምሳ ስለመቋጠር ወዘተረፈ ሀሳብ ጭንቀት ከሌለበት እንዲሁም ከ5/11 ስሌት የተላቀቀ ሲቪል ሰርቫንት መፍጠር ከተቻለ ቁጭ ብሎ በተረጋጋ ሁኔታ ስለሰላም፣ ስለፍቅር፣ ስለእርቅ፣ ስለይቅርታ፣ ስለዴሞክራሲና ስለፖለቲካ ቢወራ መደማመጥ መቀባበል ይቻላል። ካልሆነ ግን ፈተናው ከባድ ነው የሚሆነው።

ኢኮኖሚው ብሔር፣ ማንነት፣ ዘውግ የለውም። የኦሮሞውም፣ የአማራውም፣ የወላይተውም ፣ ወዘተረፈ የጋር ወኪል፣ የጋራ አካፋይ ነው። የጋራ ችግር ነው። ኢኮኖሚው እንደ ጆከር ዘር፣ ማንነት ሳይለይ ሁሉንም ወክሎ ሊያጫውት ይችላል። የአንድነት ሆነ የንኡስ ብሔር ኃይላትን ሊወክል ይችላል። የሊበራል ዲሞክራቱንም ሆነ ሶሻል ዲሞክራቱን አልያም " አብዮታዊ ዲሞክራቱን " ያለ ልዩነት ይወክላል። ብልጽግናን፣ ኢዜማን፣ አብንን፣ የእነ አቦ ቀጀላን ኦነግ፣ እናትን፣ ወዘተረፈ ከፍ ሲልም ሀገርን ሕዝብን ያለ ልዩነት ይወክላል።

አዎ ! በዚህ ወሳኝ ሰዓት የሀገራችንን ዜጎች ለአንድነት፣ ለእርቅ፣ ለመነጋገር፣ ለመቀባበል፣ ለሰላም የሚያቀራርብ ለጊዜው (ታክቲካዊ ) እና እጃችን ላይ ከቀሩን ካርዶች ኢኮኖሚው አንዱ ነው። ምንከተለው ፖለቲካዊ ስርዓት በማንነት ላይ የተመሰረተው ፌደራሊዝም ይሁን በግለሰብ መብትና ነፃነት የተዋቀረው ሊበራል ዴሞክራሲ ወይስ ራሱን ሶስተኛ አማራጭ ብሎ የሚጠራ ይሁን ኢኮኖሚው ሁሉን ወክሎ ማጫወት፣ መጫወት ይችላል።

ይሄው መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ችግር በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ከመጣው የሕዝብ ብዛት ዕድገት፤ ከአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን ፤ ከንግድ ስርዓቱ መረን የለሽነት፤ ከገብያ ስርዓቱ የተራዘመ ሰንሰለት፤ ከሕገ ወጥ ድለላ ጋር አብሮ፣ አድሞ ኢኮኖሚውን ፅኑ ታማሚ አድርጎታል። በዚህ የተነሳ የኑሮ ውድነቱ በሰዓታት፣ በቀናት ልዩነት ጣራ እየነካ ነው። የስራ አጡ ቁጥር እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እየደረሰ ይገኛል። የእነዚህ ሁሉ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሁሉ ድምር ቅርሻ በሆነ ፖለቲካዊ ቀውስ እያለፍን ነው።

እስካሁን እዚህም እዚያም ያስተዋልናቸው ግጭቶች ለዓመታት ሲቀነቀን ከኖረው የልዩነት ተረክ በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ቀውሱን ተከትለው የተከሰቱ ማህበራዊ ቀውሶች ለመሆናቸው ሞራ ገላጭ መሆን አይጠይቅም። የተሳሳተው ፖለቲካዊ አመራር ለኢኮኖሚያዊ ቀውስ ዳርጎናል። ኢኮኖሚያዊ ቀውሱ ማህበራዊ መፍረክረክን አስከትሏል። መላ ካልተበጀለት በዚህ ይቆማል ተብሎ አይጠበቅም። ወደለየለት የፀጥታ፣ የደህንነት ስጋት ሊሸጋገር ይችላል። ይህ ከመሆኑ በፊት ከገጠመን ምስቅልቅል በጊዜ ለመውጣት መስራት አለብን። ከዚህ ለመውጣት ደግሞ ዜጋው፣ መንግስት፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሲቪል ማህበራት ከፖለቲካው ይልቅ ኢኮኖሚው ላይ በአንድነት ሊረባረቡ ይገባል።

ሻሎም !

አሜን።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# «የምሰራው ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ነው»

**ሃጂ ከማል አብዱላኪም**
**የቲም ሕጻናት እንክብካቤ ማዕከል መስራችና ስራ አስኪያጅ**

**እፀገነት አክሊሉ**



“ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሃምሳ ሰው ጌጡ “ ይባላል የመረዳዳትን አይተኬ ሚና ለመግለጽ፤ አዎ የትኛውም ችግር ቢሆን ከተረዳዱበት አይጎዳም ቢጎዳም መልሶ ለማንሰራራት እድልን ይሰጣል። ይህ መረዳዳት ደግሞ እንደ ኢትዮጵያዊ ዘመናትን አብሮን የተገሻገረ የኖርነውና እየኖርነው ያለ መሰረታችን ነው።

ክርስትናውም ይሁን እስልምናው ሃይማኖቶች ሁሉም የሚያዙት እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ፣ተረዳዱ የተራበን አብሉ፣የታረዘውን አልብሱ፣አባት እናት የሌላቸውን ልጆች ጎብኙ ለቁም ነገርም አድርሱ ነው። ይህንን ሃይማኖታዊ አስተምሮ ስንቶቻችን እንተገብረዋለን የሚለውን ለራሳችን ትተን ነገር ግን ባመኑበት እምነት ብሎም በኖሩበት ቤተሰብና ኀብረተሰብ ይዘውት የመጡትን የመረዳዳት አንዱ ለአንዱ የመኖርን አስፈላጊነትና ጥቅም በተግባር ያሳዩ ለብዙዎች ተስፋ ከተስፋም አልፈው እንጀራ የሆኑ ብዙዎች ናቸው።

ልጆች ወላጅ አሳዳጊ በማጣታቸው እንዳይራቡ፤ እንዳይጠሙ፤ እንዳይታረዙ አልፎ ተርፎም ከሕልማቸው እንዳይቀሩ ብዙ የለፉም እየለፉ ያሉም አሉ ። ይህ ስራቸው ደግሞ ባመኑበት እምነት ከፍ ያለ ዋጋን የሚያሳጣቸው ከመሆኑም ባሻገር እንደ ዜጋ የሚያስመሰግን፤ ብሎም ሽልማት የሚያሰጥ መልካም ተግባር መሆኑንም መዘንጋት የለበትም።

የዛሬ የሕይወት ገጽታ አምድ እንግዳችን ለኔ የሚሉት ነገር የሌላቸው ይልቁንም ከልጅነታቸው ጀምሮ ይዘውት በመጡት የመረዳዳትና የደግነት ባህል እየተመሩ ለብዙዎች የመኖር ምክንያት የሆኑ ናቸው። እሳቸው ከተወለዱበት የትውልድ ቀያቸው አንስተው አሁን እስከሚኖሩበት አዲስ አበባ ከተማ ድረስ በርካታ ሕጻናትን ለወግ ማእረግ አብቅተዋል፤ ብቸኛ እናቶችንም ራሳቸውን አስችለው ከጥገኝነት አውጥተዋል።

“የቲም” በእስልምና ሃይማኖታዊ ትርጉሙ አባት የሌለው ልጅ ማለት ነው። እዚህ ላይ ግን አባትም ኖሮ ሰርቶ ወጥቶ ወርዶ ቤተሰቡን መመገብ ማልበስ በጠቅላላው ማስተዳደር ካልቻለ የወለዳቸው ልጆች የቲም ይባላሉ። ሃጂ ከማል አብዱላኪም ደግሞ “የቲም ሕጻናት እንክብካቤ ማዕከል” መስራችና ስራ አስኪያጅ ናቸው።

ሀጂ ከማል ከፈጣሪ በተሰጣቸው የደግነትና ለሌሎች የመኖር ጸጋን ተጠቅመው የሀይማኖትና የዘር ልዩነት ሳያሳስባቸው ብዙ የቲም ሕጻናትን ብሎም እናቶችን ከገጠር እስከ ከተማ ድረስ ከችግር እያወጡ ራሳቸውን እያስቻሉ፤ እያስተማሩ፤ እያስመረቁ ከአገር ውስጥ እስከ ውጪ አገር ድረስ በትልልቅ ስራዎች ላይ እንዲገኙ ድልድይ የሆኑ ታላቅ አባት ናቸው።

ሀጂ ከማል ተወልደው ያደጉት አርሲ ሮቤ ሰዲቃ በሚባል አካባቢ ነው። ከሁለት ታላላቅ እህቶቻቸው ቀጥለው በሶስተኛነት የተወለዱት ሀጂ ከማል እጅግ በጣም ሰፊ ቤተሰብ ውስጥ ስለማደጋቸው ይናገራሉ።

“.......ቤተሰባችን የሼህ ቤተሰብ ነው፤ እናትና አባቴ ዘጠኝ ልጆችን የወለዱ ቢሆንም ቤተሰባችንን ተቀላቅሎ የሚኖረው ግን ስፍር ቁጥር የሌለው ሰው ከመሆኑ የተነሳ በጣም ሰፊ ቤተሰብ ያለን ነን” ይላሉ ።

አባታቸው ሼህ ፈቂ በከተማው በጣም የታወቁ፤ በማኅበረሰቡ ውስጥም እጅግ ተሰሚነት ያላቸው፤ ከሌሎች ሼህ ወንድሞቻቸው ጋር በመሆን በአንድ አካባቢ ላይ ተወስነው መኖር የማይችሉ በየአካባቢው እየዞሩ በርካቶችን ሀይማኖታዊ ትምህርት የሚያስተምሩ ለእምነታቸው የቀኑ ነበሩ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ወደ ልጆቻቸውም ተጋብቶ እነ ሀጂ ከማልም ሀይማኖታቸውን አጥብቀው የሚወዱ ብሎም እንደ አባት አጎቶቻቸው በሁለም ነገር ለብዙዎች የመትረፍ ልምድን ያካበቱ ሆነዋል።

“........እኔ በቤተሰቦቼ ቤት ስኖር የተቸገረን ማብላት፤ የታረዘን ማልበስ ግዴታ እንደሆነ እየተነገረኝና በተግባርም እያየሁ ነው ያደኩት። ለምሳሌ አያቴ ሁልጊዜ ዓርብ ዓርብ አርደው ምስኪኖች እንዲበሉ፤ መንገደኞች አረፍ ብለው በልተው እንዲሄዱ ያደርጉ ነበር” በማለት ሁኔታውን ያስታውሳሉ።

**የበጎ አድራጎት ስራ በጣም ከባድ ሚስጥር ጠባቂነት የሚጠይቅ ታማኝነት፤ ሀቀኝነትን የሚፈልግ ነው**

ሀጂ ከማል እንደ ማንኛውም የአካባቢያቸው ልጆች ከብት በመጠበቅ ከእኩዮቻቸው ጋር በመቦረቅ ያሳለፉ ናቸው፤ ነገር ግን በዚህ ሂደት ውስጥ እሳቸውን ለየት ያደርጋቸው የነበረው ነገር በጨዋታቸውም ሆነ በእረኝነታቸው ወቅት የተቸገሩ ሰዎችን ሲያዩ ለመርዳት ያላቸው ጉጉት ነው።

“.....እኔ እረኛ ሆኜ ከብት ስጠብቅ የቤተሰቦቼን ከብቶች ብቻ አልነበረም የምጠብቀው ጓደኞቼን በማስተባበር የአካባቢውን ነዋሪዎች ከብቶች ሁሉ ጠብቀን ማታ በየቤታቸው አስገብተን ነበር የራሳችንን ይዘን የምንሄደው፤ ሌላው ደግሞ በእኛ ቤት ንብ የማነብ ስራ ይሰራ ስለነበር ማር በሚቆረጥበት ጊዜ ለሙስሊም ክርስቲያን ጎረቤቶቻችን ማር ለማድረስ በጉጉት ነበር የምንጠብቀው፤ ከዛም መንደሩን ሙሉ ስናድል ነበር የምንውለው “ በማለት ከቤተሰቦቻቸው ያዩት ደግነት ዛሬ ላይ ለሚሰሩት ስራ ትልቅ መደላደልን እንደፈጠረላቸው ያብራራሉ።

ሀጂ ከማል በሀይማኖት ትምህርት በቋንቋ በሼሪያ ሕግ ዙሪያ ሳውዲ አረቢያና ግብጽ በመሄድ የተለያዩ ኮርሶችን ወስደዋል። አዲስ አበባ ከመጡም በኋላ ቅዱስ ቁርአን ከሚባል ድርጅት ጋር ይሰሩ እንደነበር የሚያስታውሱት ሀጂ ከማል ነገር ግን የራሳቸው የሆነ ነገር ኖሯቸው ችግረኞችን የመርዳት ምኞታቸው ላቅ ያለ እንደነበር ያስታውሳሉ።

ሀጂ ከማል ከልጅነታቸው ጀምሮ ሰውን መርዳት መደገፍ የሚያስደስታቸው ናቸው። በዚህም የእሳቸውንም ሆነ የቤተሰቦቻቸው ተሰሚነትና ተቀባይነት በመጠቀምም የትውልድ ቀያቸው ላይ ዘመን ተሻጋሪ ስራዎችን አከናውነዋል።

በትውልድ መንደራቸው ከተማ ላይ ሰፊ ቦታን የያዘ ትምህርት ቤት ሕብረተሰቡን በማስተባበር ያሰሩ ሲሆን ከአዲስ አበባ ደግሞ አልባሳት የቁርአንና ሌሎች ዓለማዊ እውቀትን የሚያስጨብጡ መጽሀፍትን በማሰባሰብና ይዞ በመሄድ ትምህርት ቤቱ አገልግሎት እንዲሰጥ ስለማድረጋቸው ይናገራሉ። በሌላ በኩልም በዛው በአካባቢያቸው ላይ ላሉ መስኪዶች በወረዳ ደረጃ እንዲደራጁ በማድረግና ሀይማኖታዊ አገልግሎትን ለመስጠት ያስፈልጓቸዋል የሚሉትን ግብዓት በማሰባሰብ እንዲከፋፈሉ የማድረግ ተግባርንም ከውነዋል።

“.......እኔ ለስራው የተፈጠርኩ ይመስለኛል፤ ከበፊትም ጀምሮ የአካባቢዬ ነዋሪዎች ለእኔ ትልቅ እምነትና ፍቅር አላቸው፤ እኔም እነሱን አስተባብሬ ይህንን አምጡ ከማለት ባሻገር መስኪዱንም ትምህርት ቤቱንም እየሰራሁ አሳያቸዋለሁ፤ ይህ ደግሞ በጣም ስለሚያስደስታቸው በቀጣይ ይህንን እንስራ ስላቸው እምቢ የሚል አይኖርም። ይህ ነገር ደግሞ እያደገ ሲሄድ አገልግሎቱም እየሰፋና ብዙዎችን ተጠቃሚ እያደረገ መጣ “ይላሉ።

ሀጂ ከማል በትውልድ አገራቸው ላይ ያለውን የወፍጮ ቤት ችግር ለመቅረፍ አዲስ አበባ ካሉ ባለጸጋ 27 ወፍጮዎችን በመጠየቅና በየመስኪዱ እንዲተከሉ በማድረግ እናቶች የወፍጮ ችግራቸው እንዲቀረፍ ከፍ ያለ ስራንም የሰሩ ታላቅ ሰው ናቸው።

ሀጂ ከማል “ መስጠት መሰጠት ሆኖላቸዋል” አምላክ የሰጣቸውን የመስጠት በረከት እሳቸውም መንዝረው ስለተጠቀሙበት ዛሬ ላይ ለብዙዎች ተስፋ ከመሆናቸውም በላይ እሳቸውም በሰሩት ስራ ላቅ ያለ ክብር አግኝተው የሚኖሩ ናቸው ።

ይህ ደግነታቸው በጣም በሕዝቡ ውስጥ የገባ ከመሆኑ የተነሳ በእንግድነት እንኳን አገራቸው ሲሄዱ ነዋሪው የሚሰጣቸው ፍቅር ያስገርማቸዋል። ”.......እኔ የቲምን ከማቋቋሜም በፊት ቢሆን ለበዓል ከአዲስ አበባ አርሲ ስሄድ ለአሮጊት ሽማግሌው ዣንጥላ ካፖርት ለሴቶች የሚያስፈልጋቸውን ብቻ አቅሜ የቻለውን ሁሉ በሻንጣዬ ሞልቼ ነበር የምሄደው። ስመለስ ሻንጣዬ ባዶውን ነው የሚመጣው። ከለበስኩት ልብስ ውጪ የሚተርፈኝም ነገር አይኖርም “ በማለት ሁኔታውን ይገልጻሉ።

**የቲም የሕጻናት እንክብካቤ ማዕከል**

ማዕከሉ በ1993 ዓ.ም ልበ መልካምና የድሆች አባት በሆኑት ሀጂ ከማል ሀሳብ አመንጪነት በሁለት ሰራተኛና በ50 የቲም ሕጻናት የተመሰረተ ነው። ስራውን ሲጀምሩም እኔ ራሴን ልስጥ ግን ደግሞ የቲም ሕጻናትና የተጎዱ እናቶች ቀን ይውጣላቸው በችግር ኖረው አይሙቱ ብለው ነበርና ከዛ በኋላ ድርጅቱን በሁለት እግሩ አቁመው አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ ለማድረስ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል።

“.......አንዳንድ ሰዎች የሕጻናትም ይሁን የሴቶች መርጃ ድርጅቶችን ሲመሰርቱ መጀመሪያ የሚሉት ራሴንና ቤተሰቤን ላቋቁም ነው። ይህ በጣም የተሳሳተ ብሎም የማይሆን አካሄድ ነው። ለምሳሌ አንድ ተክል ተተክሎ ተገቢውን እንክብካቤ ሳይደረግለትና አስፈላጊውን ትኩረት ሳይሰጠው እደግ ቢባል ውሎ አድሮ ደራቂ፤ ከሳሚ ነው የሚሆነው፤ ይህ ስራም እንደዛው ነው። አንድ ሰው ወደስራው ገብቶ ቆይ ለራሴ ቤት ልስራ፤ መኪና ልግዛ ዘመዴን ቤተሰቤን ላቋቁም ካለ ነገሮች እዛው ላይ ከስመው ነው የሚቀሩት” በማለት ተሞክሯቸውን ይናገራሉ።

እኛ ስራውን ለመስራት ልጆችን ከችግር አላቀን ተምረው ጥሩ ዜጋ እንዲሆኑ ለማድረግ የብዙዎችን ደጅ መጥናት ይጠበቅብናል፤ እነዛ ረጂ አካላት ደግሞ የሰጡት ገንዘብ ቁምነገር ላይ ውሎ ሲያዩ ነገም ለመስጠት ይበረታታሉ፤ የቲም ሕጻናት መንከባከቢያ ማዕከልም ያገኘውን ሁሉ ልጆቹ ለእናቶቹ ላይ በማዋል ከፍ ያለ ውጤትን ያስመዘገበ ተቋም በመሆኑ ዛሬ ላይ በአንድ የስልክ ጥሪ ብቻ ብዙ እርዳታን ማግኘት የሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል ይላሉ።

ሀጂ ከማል ስለ ስራው ሲናገሩ የበጎ አድራጎት ስራ በጣም ከባድ ሚስጥር ጠባቂነት የሚጠይቅ ታማኝነት፤ ሀቀኝነትን የሚፈልግ ነው ። አንዳንድ ጊዜ ረጂ አካላት ጥሬ ገንዘብን በማታ በፌስታል ሰጥተው ሊሄዱ ይችላሉ፤ ይህንን ገንዘብ እስከሚነጋ ድረስ በታማኝነት ጠብቆ ማስቀመጥ ትልቅ እድለኝነትንም ይጠይቃል እኔ በዚህ ውስጥ ያለፍኩ ነኝ ይላሉ።

“.......እኔ የቲምን ስመሰርት አብረን ፍቃድ ያወጣነው 13 ነበርን። ነገር ግን የታማኘነቱን ኬላ ማለፍ ተስኗቸው ብዙዎቹ በያሉበት ተንጠባጥበዋል። ግማሾቹ ከስመዋል ግማሹም ለራሱ ማረፊያ ቢሮ እንኳን ሳይኖረው በየሜዳው ይዞራሉ፤ እኔ ግን አባት አያቶቼ ባስተማሩኝ ሀቀኝነትና ታማኝነት እዚህ ደርሻለሁ። ዛሬ ከአገር አልፈን አለማቀፍ እውቅናና ተቀባይነት ያለን ብዙ የሚያግዙን ሰዎችን ማፍራት የቻልን ሆነናል “በማለት ይናገራሉ።

አሁን ላይ ድርጅቱ ባሳየው ውጤት ከጀርመኖች፣ከእንግሊዞች፣ከቱርኮች፣ከአረብ ኤምሬት፣ከዴንማርኮች ጋር ጠንካራ ግንኙነትን መስርቶ

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## «የምሰራው ስኢትዮጵያውያን...

ከገጽ 7 የዞረ

በመስራት ላይ እንደሚገኙ ሃጂ ከማል ያስረዳሉ።

"........ሰው ለሚሰራው ስራ ታማኝ ከሆነ ከሰጪ፤ ከመንግስት እንዲሁም ከራሱም ጋር አይጣላም። ነገር ግን በደሃ ስም ራሴን አበለጽጋለሁ ብሎ ከተነሳ ከሁሉም ጋር ከመጣላቱም በላይ ስራውም ዘላቂነት አይኖረውም "ይላሉ።

ሀጂ ከማል በ23 ዓመት የስራ ዘመናቸው በርካታ አስደሳች፤ አሳዛኝ አንዳንድ ጊዜም ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች አጋጥመዋቸው ያውቃሉ፤ ነገር ግን የተፈጥሮ ለጋስነታቸው ሩሁሩህነታቸው ብሎም ለሚሰሩት ስራ ከፍ ያለ ታማኝነት ያላቸው በመሆኑ ሁሉንም ተሻግረው ዛሬ የቆሙበት ደረጃ ላይ ለመድረስ አላቃታቸውም።

ከብዙ ስራዎቻቸው መካከል የማይረሷት አንድ እናት አለቻቸው፤ "....... ባሌ አካባቢ ናት፤ ሴትየዋ 6 ሄክታር መሬት አላት፤ ስምንት ልጆችንም የማስተዳደር ኃላፊነቱ እሷ ላይ የወደቀ ነው፤ ነገር ግን አንድ ኪሎ እህል በቤቷ የለም፤ ሄደን ጠየቅናት ምንድነው ችግርሽ አልናት በሬ፣ዘር፣ማዳበሪያ እያለች ችግሯን አስረዳች፤ በዚህ ወቅት ሁለት በሬዎች፣ሶስት ኩንታል፣ማዳበሪያ ሶስት ኩንታል ዘር ገዛን፤ አራት ኩንታል የዓመት ቀለብ የሚሆናትን እህል ገዛሁና በይ ስራ ስሪ አልኩ፤ በተሰጣት ስጦታ ሰርታ በዓመቱ 47 ኩንታል ስንዴና 7 ኩንታል ባቄላን ማምረት ቻለች። አሁን ሶስት ዓመት ሊሆናት ነው። ምርቷም በዛው ልክ በእጥፍ እያደገ ሴትየዋና ልጆቿም በከፍተኛ ሁኔታ ዘካዋን እያወጣች ትኖራለች" በማለት የስራቸውን ውጤት ይናገራሉ።

ከገጠር ባሻገር በአዲስ አበባ ከተማ 670 ልጆችን በአራዳ፣ጉለሌና አዲስ ከተማ ክፍለ ከተሞች ያግዛሉ። "......ከተማው ላይ ልጆቹ ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ ከፍ ያለ ትኩረትን እንሰጣለን፤ እስከ አሁንም 360 ልጆች ትምህርታቸውን በአግባቡ ተምረው ከድርጅቱ ወጥተዋል፤ አሁንም ከመቶ በላይ ልጆች ዩኒቨርሲቲ ገብተዋል። ነገር ግን ከተለያዩ ክልሎች ምንም ሰብሳቢ አጋዥ በማጣታቸው ምክንያት በድርጅቱ ውስጥ ማደሪያና መሰረታዊ ነገሮች ተሟልቶላቸው የሚማሩ ልጆች አሉን" ይላሉ።

አዲስ አበባ ከተማ ላይ 284 እናቶችን በመመዝገብ ኮንደምንየም ቤት ምዝገባቸውን በመክፈል መጠለያ እንዲያገኙ ተደርጓል። ቤት ቦታ ኖሯቸው የሚሰሩት ነገር ላጡ እናቶች ደግሞ ከጉሊት ጀምሮ ሱቆችና የተለያዩ በቤት ውስጥ ተሰርተው ገቢ ሊያመጡ የሚችሉ ስራዎችን እንዲሰሩ እየተደረገ ሲሆን በቀጣይም ከመንግስት ስራ አስፈጻሚዎች ጋር በመነጋገር ችግረኛ የሆኑ ሴቶች በአንድ ላይ ሼድ እንዲያገኙና እኛም እንድናግዛቸው እየሞከርን ነው።

አንድ እንዲታወቅ የምፈልገው ነገር ይላሉ ሀጂ ከማል በገጠርም ሆነ በከተማ የሚሰሩ ስራዎች ሰጥቶ መሄድ ብቻ ሳይሆን ሰዎቹ በተሰጣቸው ነገር ምን ያህል ፍሬ አፈሩ ተማሪዎች በምን መልኩ ነው ለትምህርታቸው ትኩረት እየሰጡ ያለው የሚለው ጥብቅ ክትልል ይደረግበታል፤ እናቶችም የባንክ ደብተር ከፍተው ገንዘብ እንዲቆጥቡ ይደረጋል ።

በሌላ በኩልም በገጠር አካባቢ ያሉ ሴቶች የወር አበባቸው በሚመጣበት ጊዜ አስፈላጊው የንጽህና መጠበቂያ ስለማይኖራቸው ከትምህርት የመቅረት የመሳቀቅ ሁኔታ አለና ድርጅቱ ይህንን ችግር ለመፍታት 8 ሚሊየን ብር ገደማ በመመደብና ከቱርክ በጎ አድራጊዎች ጋር በመተባበር የሚታጠብ ሞዴስ ማምረቻ ፋብሪካን በግቢው ውስጥ አቋቁሞ ምርቱን እያመረተ ለብዙዎችም የስራ እድል ፈጥሮ እየሰራ ነው።

### አብሮ የመኖር ባህላችን

ኢትዮጵያ የእስላምም የክርስቲያንም አገር ናት። ከሁሉ በላይ ደግሞ መካና ሳውዲ አረቢያ እንኳን እስልምናን ሳይቀበሉ የተቀበለች አገር ናት። ሕዝቧም ድንቅ ሕዝብ ነው። እኔም በስራዬ እስላም ክርስቲያን ይሉት ክፍፍል አድርጌ አላውቅም፤ ወደፊትም አላደርግም፤ ፈጣሪም ያለው ነብያችንም ያስተማሩን የተራበን አብሉ አጠጡ የታረዘን አልብሱ እንጂ በዘር በሃይማኖት እየከፋፈላችሁ እርዱ አላሉም። እኔ ማነኝና ነው ክፍፍል ውስጥ የምገባው። የምሰራው በሙስሊምነቴ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነቴ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ነው ይላሉ ።

በመሰረቱ የእርዳታ ድርጅት ተሁኖ ፖለቲካውም ሀይማኖቱም አይቅርብኝ ከተባለ መስራት አይቻልም። እኔ ከዚህ ነጻ ሆኜ የተቸገሩ የገጠር ልጆቸንና እናቶችን በከተማም ሁኔታዎች ያልተመቿቸውን የቲም የሆኑ ሕጻናትን ከመንግስት እየተቀበልኩ የሀይማኖት ልዩነት ሳላደርግ መስራት ነው የምፈልገው፤ እሱንም እያደረኩ ነው። እውነት ለመናገር ሌሎች ራሳቸው መጥተው እኛ ቤት የሚሰራውን ቢያዩ ትምህርት ይሆናቸዋል።

".......በነገራችን ላይ ኢትዮጵያዊ አንድነታችን ተካፍሎ የመብላት ተባብሮ የመኖር በችግር በደስታችን የመገናኘት ባህላችን ሕዝቡ ጋር እንዳለ ነው፤ ፖለቲከኞቹ ጋር ግን ጠፍቷል፤ ተበላሽቷል።የሀይማኖት አባቶች ጋርም ይህ ችግር ገባ ወጣ እያለ ነው። ከከተማም ወጣ ብለሽ ብታየ ሕዝቡ የቀደመ ፍቅርና መተባበሩ ላይ ነው፤ አብሮ ያርሳል እህል ሲደርስ ለእስላም ለክርስቲያን ብሎ አርዶ ተደስቶ በጋራ ይበላል፤ ይጠጣል፤ ልጆቹን ይድራል፤ ሀዘኑን በጋራ ይወጣል፤ እናም ፍቅሩ እንዳለ ነው። ነገር ግን ፖለቲከኞች ስራቸው ስለሆነ ፕሮፓጋንዳ ይሰራሉ። ሚዲያውም እነሱን ተቀብሎ የማይገናኝ ወሬን ያወራል፤ ይህ ቢታረም ደስ ይለኛል" ይላሉ።

ከከተማ ወጣ ተብሎ ትንሽ ኪሎ ሜትሮች መሄድ ቢቻል ሕዝቡ የድሮ እንግዳ አቀባበሉ ላይ ነው ያለው፤ ብሉ ጠጡ ማለት ያውቅበታል። እንዳልኩሽ እኛ እዚህ ቁጭ ብለን የምንሰማውና መሬት ላይ ያለው ነገር አይገናኝም የሚሉት ሀጂ ከማል አሁን እንኳን በቅርቡ ወደ ጫንጮ ሄጄ አንድ ተማሪ ጠራሁና "......አንተ ልጅ ቤተሰቦችህ አሉ እኛ ከሩቅ ነው የመጣነው፤ ተርበናል፤ የሚበላ የሚጠጣ ስጠን፤ ስንለው በጣም በሚገርም ደስታና ፈገግታ ግቡ ጠላ አለ እንጀራም በሚጥሚጣ ትበላላችሁ ወተት ብቻ ነው የሌለው ነው ያለን አንጂ አንተ እንደዚህ ነህ እንደዚያ የሚል ሀሳቡ ላይም አልመጣም። እንግዲህ ኢትዮጵያውያን ይህ ነን" በማለት የቆየው እኛነታችን አብሮን መዝለቁን ያስረዳሉ።

### ስኬት

ሀጂ ብዙዎች ቢያልሙና ቢመኙም ለጥቂቶች ብቻ የተሰጠን መልካም ስራ በመስራት ላለፉት 23 ዓመታት ቆይተዋል።በሰሯቸው ስራዎች ከገጠር እስከ ከተማ ብዙ ስኬቶችን ለማየት የቻሉ ናቸው። እሳቸው ጋር የሁለት የሶስት የአምስት ዓመት ሕጻናት ሆነው መጥተው አድገው ተምረው ዛሬ ላይ ዳኛ የሆኑ፣ ቢቢሲ የዜና ማዕከል የገቡ፣ቱርክ፣ባህሬን፣ዱባይ፣ካናዳ እንዲሁም በሌሎች የዓለም አገራት ላይ በመሄድ የራሳቸውን ስራና ኑሮ እየኖሩ ለሌሎችም እየተረፉ ያሉ ብዙዎች መሆናቸውን ይናገራሉ። በያዝነው ዓመት እንኳን ስድስት ልጆች የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት አምጥተው ዩኒቨርሲቲ ገብተዋል።

### በዓልና ሀጂ ከማል

"......እንደ በዓል ረመዳንን እወደዋለሁ፤ ምክንያቱ ደግሞ ድሮም አባቴ ቤት ሆኜ ወደዚህ ስራ ከገባሁም በኋላ ረመዳን ሲሆን ብዙ ችግረኞችን እናግዛለን፤ እናስፈጥራለን በተለይም 18 ዓመት ሙሉ ሰላሳውንም ቀን በግቢያችን ከ 650 እስከ 700 ሰው በየቀኑ እናስፈጥራለን ያ ልዩ ስሜትን የሚፈጥር ነው" ይላሉ።

በሌላ በኩልም ረመዳን ንፁግ የሆኑ የእምነቱ ተከታዮች ራሱ እጃቸው የሚፈታበት ካላቸው ለማካፈል የሚፈቅዱበት ወር በመሆኑ ለእኔ ልዩ ነው በማለት ይናገራሉ።

በነገራችን ላይ ግን አረፋ ታላቅ በዓል ነው። ሙስሊሞችም የሚደሰቱበት ነው በእስልምናም አምስተኛ ደረጃ ላይ ያለ ትልቅ እለት ነው፤ ከዚህ ከዚህ አንጻር ደስ ይለኛል። እኔም ከወገኖቼ ጋር በመሆን በዓሉን በደስታ አሳልፋለሁ ።

### የቤተሰብ ሁኔታ

ሀጂ የቤተሰብ ሁኔታቸውን ለመግለጽ በጣም ነው የሚከብዳቸው፤ የሚከብዳቸውም ብቻ ሳይሆን እንባ ይቀድማቸዋል፤ ለዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ ከወለዷቸው በላይ እሳቸውን አምነው ተማምነው አባዬ እያሉ አስር እስራቸው የሚሉት የቲም ልጆች ውስጣቸውን ስለሚያንሰፈስፉት ነው፤ አዎ እኔም ያየሁት ይህንኑ ነው፤ ሀጂ ቢሯቸው ባለበት ሰባራ ባቡር አካባቢ ያለው የቲም ሕጻናት እንክብካቤ ማዕከል ውስጥ ያሉት ልጆች ሲያዩቸው ፊታቸው ይበራል። አባት አለን የሚለው ስሜታቸው ከፊታቸው ይነበባል፤ አባ እያሉ ይጠሯቸዋል፤ የሚፈልጉትን ነገር ይጠይቋቸዋል



የከፋቸውን ያማክሯቸዋል። ሀጂም በምላሹ ሊሟላላቸው የሚገባው አሟልተው፤ አማክረው የትምህርት ውጤታቸውን ተከታትለው የደከመውን አበረታተው የጎበዘውን ሸልመው የአባት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ ።

"........እኔ የወለድኳቸው ሶስት ልጆች አሉኝ። ነገር ግን የቲም ሕጻናት እንከብካቤ ማዕከል ውስጥ ከ 30 በላይ ሕጻናት በቋሚነት ይኖራሉ፤ እነዚህ ልጆች አላህ የሰጠኝ ልጆቼ ናቸው "ባባ" ብለው ከትምህርት ቤት ሲመጡ አቅፈው ስመውኝ ውሏቸውን ሲነግሩኝ ልቤ ይነካል፤ እውነት ለመናገር ቤቴን አላውቀውም፤ እዚሁ ከእነሱ ጋር ነው የምውለው፤ ይህ ደግሞ በጣም ደስተኛ አድርጎኛል፤ እነዚህን ልጆች ከወለድኳቸው ልጆቼ ማበላለጥም ይህንን ያህል ልጆች አሉኝ ብሎ ማለትም በጣም ይከብደኛል " በማለት ከእንባ ጋር ይናገራሉ።

ሀጂ የወለዷቸውን ልጆች እንደሚያሳድጓቸው ልጆች ትኩረት አይሰጧቸውም። ምክንያቱም እነሱ እናታቸው የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ ሊያሟሉላቸው ይችላሉ ብለው ስለሚያምኑ ነው፤ እየሆነም ያለው እንደዛው ነው።

"....... እኔ ስለ አረፋ በዓል አከባበር ሳስብ ስለ ሶስት የአብራኬ ክፋይ ልጆቼ ብቻ ሳይሆን ስለ ሺዎች የቲም ሕጻናት ነው የማስበው፤ በምን መልኩ ነው እነሱን አስደስቼ በዓል የማከብረው የሚለው ነው የሚያስጨንቀኝ " ይላሉ።

መጀመሪያ አካባቢ ስራው በጣም ይከብዳቸው እንደነበር የሚናገሩት ሃጂ ከማል ምክንያታቸው ደግሞ ሀጂ የብዙዎች መሆናቸውና ጊዜና ገንዘባቸውን ለቤቴ የማይሉ ለጋስ አባወራ መሆናቸው ነበር። ይህ ደግሞ በተለይም መጀመርያዎቹ አካባቢ ለባለቤታቸው በጣም ፈታኝ ነበር።

"......ባለቤቴ መጀመሪያ አካባቢ እንግዳ ሲበዛበኝ ከድርጅቱም አልፎ ስራው ቤቴ ድረስ እየሄደ ብዙዎች ቤት ማደር መዋል ሲጀምሩ በጣም ይከብዳት ነበር፤ ነገር ግን እኔ ፈጣሪዬንም ለምኜ ለእሷም እኔ ከሰፊ ቤተሰብ ነው የወጣሁት ብቻዬን መብላትም መኖርም አልችለም እንደውም ቀን 16 ሰው ምሳ ቤት እንዲበላ ማታም በተመሳሳይ 14 ሰው እራት እንዲበላ እፈልጋለሁ በማለት ቁርጡን ነግሬ ሙሉ ትኩረቴን ስራዬ ላይ ነው ያደረኩት።አሁን ፈጣሪ ይመስገን ከእኔ ይበልጥ ለስራዬ የምትጨነቅ ልጆቼንም ከእኔ በላይ የምትወድና የምትንከባከብ ሆናለች" በማለት ያስረዳሉ።

ዛሬ ላይ ባለቤታቸው ልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን አስቤዛ በማድረግ ልብስ ጫማቸውን በመግዛት የትምህርት ቤት ክፍያ በመክፈልና ውጤታቸውን በመከታተል ብቻ ለድርጅቱ ቀኝ እጅ ሆነው የባለቤታቸውን የበጎ ስራ እየደገፉ አብረው እየኖሩ ነው።

**ከገጠር ባሻገር በአዲስ አበባ ከተማ 670 ልጆችን በአራዳ፣ ጉለሌና አዲስ ከተማ ክፍለ ከተሞች ያግዛሉ**

# ባህልና ቱሪዝም

# የኢትዮጵያ እስላማዊ ቅርሶች

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ በዓለም በሀይማኖት፣ በባህልና በልዩ ልዩ እሴቶች ሀብት በቀዳሚነት ከሚጠቀሱ አገራት ትመደባለች። በተለይ በሀይማኖቱ ረገድ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠሩና ጥንታዊ መሰረት ያላቸውን ተቋማት በውስጧ ይዛለች።

ከእነዚህ ሃይማኖቶች መካከል ሕዝባዊ መሰረታቸው ሰፊና ጠንካራ የሆኑት የክርስትናና እስልምና ሃይማኖች ይጠቀሳሉ። የእምነቶቹ ተከታዮች ቁጥር መብዛት ብቻ ሳይሆን፣ በባህልና፣ በታሪክ፣ በቅርስ እንዲሁም በዜጎች የእለት ተእለት የኑሮ ዘይቤ ላይ ባሳደሩት በጎ ተፅእኖም በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ።

ኢትዮጵያ ካሏት ቅርሶች ውስጥ አብዛኛዎቹ ሀይማኖታዊ መሰረት አላቸው። ከእነዚህ መካከል ደግሞ እስላማዊ ቅርሶች ይገኙበታል። እስልምና በኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናትን የተሻገረ ታሪክና አሻራ ያለው መሆኑን አጥኚዎች በተለያዩ መረጃዎቻቸው፣ ምርምሮቻቸውና ማስረጃዎቻቸው ያመለክታሉ። ከአስተምሮቱ ባሻገርም ለታሪክ ለትውልድ የሚተላለፉ የአገር ሀብቶችና የእስልምናን መሰረት የሚያወሱ ቅርሶች በኢትዮጵያ ለዓለም ማበርከት እንደተቻለ እነዚሁ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ።

በኢትዮጵያ በሃይማኖትና ባህላዊ ይዘቱ የሚታወቀው በምስራቁ የሐረሪ ክልል በድምቀት በየዓመቱ የሚከበረውን ሸዋል ኢድ በአልን በዚህ ዓመት የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ከዓለም የማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል አንዱ አድርጎ መመዝገቡ ይታወሳል። ይህ ስኬት ሌሎች በኢትዮጵያ የሚገኙ እስላማዊ ቅርሶች በስፋት እንዲታወቁ በር እንደሚከፍት ይጠበቃል። በመሆኑም ምሁራን፣ የዘርፉ ተመራማሪዎችና ዘርፉን የሚመራው የመንግስት ባለድርሻ አካል ቅርሶቹ እንዲለሙ፣ እንዲተዋወቁና የጎብኚዎች መዳረሻ እንዲሆኑ በስትራቴጂ የተደገፈ የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በኢትዮጵያ ቅርሶች ላይ ልዩ ትኩረት አድርገው ምርምር የሚያደርጉ፣ ጥናታዊ ፅሁፎችን በልዩ ልዩ ጆርናሎች ላይ የሚያትሙ እንዲሁም የመስህብ ሀብቶቹ የዓለምን ትኩረት እንዲስቡ ባገኙት መድረኮች ላይ የሚሞግቱ ምሁራንም አሉ። ከእነዚህ መካከል እስላማዊ ቅርሶች ላይ ልዩ ትኩረት አድርገው ለዓመታት የሰሩም ይገኛሉ።

ባሳለፍነው ወር የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን አንደኛውን የኢትዮጵያ ዓመታዊ ቅርስ ምርምር ጉባኤ ባካሄደበት ወቅት የጥናት ውጤቶቻቸውን ካቀረቡት መካከል አንደኛው በኢትዮጵያ የሚገኙ እስላማዊ ቅርሶች ላይ ስራቸውን አቅርበው ነበር።

ረዳት ፕሮፌር አህመድ ዘካሪያ የታሪክ ተመራማሪ ሲሆኑ፣ ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2006 ዓ.ም በእስልምናና በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ባህላዊና ሀይማኖታዊ ቅርሶች ላይ የሰሩ ምሁር ናቸው። ረዳት ፕሮፌሰሩ በተለይ የኢትዮጵያን የእስልምና ቅርሶች በሚመለከት ሰፋ ያሉ ጥናቶችና ምርምሮችን አድርገዋል። እርሳቸው እንደሚሉት፤ አፍሪካ ውስጥ አሉ ከሚባሉት ጥንታዊና የመጀመሪያ መስኪዶች መካከል አል ነጃሺ ቀዳሚው ነው። ይሁን እንጂ ይህንን ቅርስ ለመጠበቅ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተገቢው መንገድ ለማስተዋወቅ በቂ ስራዎች አልተሰሩም። በዚህ ምክንያት ሌሎች አገራት የታሪክ ሽሚያ ውስጥ መግባታቸውን ያነሳሉ። በተለይ በሱዳን፣ በሶማሊያ እና በኤርትራ ውስጥ የመጀመሪያው መስጂድ አል-ነጃሺ እንደሚገኝ በመግለፅ የተሳሳተ ትርክት መኖሩ የዚህ ማሳያ ነው።

‹‹እስልምናና ኢትዮጵያ ተጨባጭ ትስስር አላቸው›› የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ በምሳሌነት በእስልምና ታሪክ የመጀመሪያውን አዛን ያሰማውን (የሶላት ጥሪ) ያሰማውን ቢላል አል-ሀበሺን ይጠቅሳሉ። ይህንን ታሪካዊ ሀብት ለዓለም አጉልቶ በማስተዋወቅ በቅርስነት በመመዝገብ እና በሀይማኖታዊ መስህብ ሀብትነት ለመጠቀም መስራት ተገቢ መሆኑን ያስረዳሉ።

በውጪ አገር አጥኚዎች በ1920ዎቹ አካባቢ በተደረገ ጥናት ከሐረር እስከ አዲስ አበባ ባለው ቦታ ላይ በርካታ እስላማዊ የአርኪዮሎጂ ቅርሶች ተገኝተዋል የሚሉት









ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ፤ በተመሳሳይ ከዳህላክ እስከ ሐረር በርካታ የመቃብር ቦታዎች መገኘታቸውን ያመለክታሉ። በዓለም ላይ ያሉ አብዛኛዎቹ ታላላቅ ቅርሶችም (አክሱም፣ ግብፅ እና ሌሎች) ከመቃብር ጋር የተገናኙ መሆናቸውን ያነሳሉ። በዚሁ መሰረት በኢትዮጵያ በሚገኙ የመቃብር ስፍራዎች የእስልምና ታሪካዊ መረጃና ማስረጃዎች መገኘታቸውን ይናገራሉ።

ረዳት ፕሮፌሰሩ ለበርካታ ዓመታት ባደረጉት ምርምር ጥንታዊ መስኪዶች፣ የመቃብር ስፍራዎች የእስልምናን ታሪክ፣ የሃይማኖቱ ተከታዮቹን አሰፋፈር እንዲሁም ሌሎች የታሪክ እና የባህል ሀብቶች መለየት መቻላቸውን ይገልፃሉ። በተለይ በአፋር፣ በሐረሪ፣ በድሬዳዋ፣ በሶማሌ እና ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች እነዚህ እስላማዊ ቅርሶች በስፋት እንደሚገኙም ያስረዳሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ስፍራዎች በቂ ጥበቃ፣ እንክብካቤ አለማግኘታቸውን ያስረዳሉ።

በዓለም ቅርስነት ከተመዘገበው የሐረር ጀጎል ግንብና በከተማዋ ውስጥ ከ83 በላይ ጥንታዊ መስጂዶች እንደሚገኙ የሚናገሩት ረዳት ፕሮፌሰሩ፣ በክልሉ በአጠቃላይ እስላማዊ ቅርሶች፣ ታሪካዊ ስፍራዎችና የመስህብ ቦታዎች በብዛት እንደሚገኙ ይጠቁማሉ። ከዚህ ባሻገር በኢትዮጵያ እንደ ድሬ ሼህ ሁሴን፣ የመውሊድ ክብረ በዓል እና ሌሎችም እስላማዊ የሆኑ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች በዓለም ቅርስነት የመመዝገብ አቅም እንዳላቸው በመግለፅ ኢትዮጵያን ሊያስተዋውቁ የሚችሉ እምቅ ሀብት መሆናቸውን ይናገራሉ። በተለይ ዛሬም ድረስ ውበት፣ ታሪክ እና ትውፊቱን ጠብቆ የቆመው ድሬ ሼህ ሁሴን በዓለም ቅርስነት መመዝገብ ያለበት ታላቅ ቅርስ መሆኑን ረዳት ፕሮፌሰሩ ይገልፃሉ።

መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ ይህ ስፍራ ይህ ስፍራ በ11ኛው ክፍለ ዘመን የተገነባ እና ዛሬም ድረስ በውበት ቆሞ የዚያን ጊዜውን እውቀት የሚናገር ቅርስ ነው። በጊዜው የእስልምና ሃይማኖት መሪ የነበሩት አባት ድሬ ሼህ ሁሴን ይህን ስፍራ በውብ ጥበብ ማስገንባታቸውንም መዛግብት ያስረዳሉ።

በድሬ ሼህ ሁሴን መስኪድ የእስልምና ሃይማኖትን በማስተማር ብዙ የእምነቱ ተከታዮችን በሃይማኖቱ ስርአት እና ሕግጋቶች እንደታነፁ መረጃዎች ያመለክታሉ። ሼህ ሁሴን የእስልምና ሃይማኖትን ከማስተማር ጎን ለጎንም በዚህ ስፍራ ላይ ሰው ሰራሽ ሃይቅን የመገንባት፣ በእርከን ስራ ተራሮችን የማልማት እና ከብሄር ብሄረሰቦች ጋር በመተባበር እና በመዋደድ በአብሮነት የመኖር ብሂልን ይመሩ የነበሩ አባት መሆናቸውን፤ በተጨማሪ ሳይንስ

**‹‹የኢትዮጵያን ቅርሶች፣ ባህሎችና ታሪኮች ጠብቆ ለትውልድ ከማስተላለፍ ባሻገር ለቱሪዝም በምን መልኩ መጠቀም እንደሚገባ ስትራቴጂ ሊነደፍ ይገባል››**

አዋቂ እና አርቀው አሳቢ መሪ እንደነበሩ መዛግብት ያስረዳሉ።

‹‹የኢትዮጵያን ቅርሶች፣ ባህሎችና ታሪኮች ጠብቆ ለትውልድ ከማስተላለፍ ባሻገር ለቱሪዝም በምን መልኩ መጠቀም እንደሚገባ ስትራቴጂ ሊነደፍ ይገባል›› የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ አህመድ ዘካሪያ፤ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ ሰነድ ከማዘጋጀት፣ እና ቅስቀሳ ከማድረግ ባሻገር በቅድሚያ ቀጥታ ማህበረሰቡ እንዲያውቀው፣ እንዲጠቀምበትና በሀብቱ የኔነት እንዲሰማው ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ። ይህንን መተግበር ከተቻለ በቀላሉ የዓለም ቅርስ ዝርዝር ውስጥ ማስገባትና የቱሪዝም መስህብ ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ ቀጣዩ ቀላል ስራ መሆኑን ይገልፃሉ። እስላማዊ ቅርሶችም ይህንን መንገድ እንዲከተሉ ማልማት፣ መጠበቅና ማስተዋወቅ እንደሚያስፈልግ ያሳስባሉ።

የእስልምና እምነት ተከታዮች ከመካ መዲና ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው በእስልምና እምነት ታሪክ ውስጥ ዋነኛው ሁነት እንደሆነ የሚያነሱት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ፣ ይህ እውነታ ኢትዮጵያን በእስላማዊ አስተምሮ፣ በታሪካዊና በሃይማኖታዊ ቅርስ እምቅ ሀብት ካላቸው አገራት ተርታ እንደሚያሰልፋት ይናገራሉ። ይህንን እድል ተጠቅሞ ቅርሶቹ ለቱሪዝም አስተዋፆኦ እንዲኖራቸው መላው ዓለምም በቂ እውቀት ስለ ኢትዮጵያ እስላማዊ ቅርስ እንዲኖረው መስራት ይገባል ይላሉ።

የታሪክ መዛግብት እንደሚያስረዱት በመካ የነበሩ ሙስሊሞች ያጋጠማቸውን እንግልት ተከትሎም ነብዩ መሐመድ ምዕመኑ ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ እንዲጠለሉ ምክር ሰጥተዋቸዋል። ይህ ሁኔታም ኢትዮጵያ በመላው ዓለም በሚገኙ ሙስሊሞች ዘንድ ልዩ ቦታ እንድታገኝ አስችሏታል። ኢትዮጵያ ጥንታዊ መስጊዶችን ጨምሮ፣ የቅዱስ ቁርአን፣ መድረሳ እና መንዙማዎችን እና የተለያዩ እስልምናን የሚገልጹ ቅርሶች ባለቤት ሆናለች። ይሁን እንጂ ልክ እንደሌሎቹ የዓለማችን ክፍሎች ጎብኚዎች በበቂ ሁኔታ ወደ አገሪቱ እየገቡ አይደለም።

ረዳት ፕሮፌሰሩ እንደሚገልፁት ኢትዮጵያ ካላት ቀዳሚ እስላማዊ ቅርስ አንዱና ዋንኛው በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተገነባ እና በአፍሪካ የመጀመሪያ እንደሆነ የሚነገርለትን የአል ነጃሺ መስጊድ ነው። ታሪካዊቷ የሐረር ከተማ በእስልምና አስተምሮ ከፍተኛ ክብር የሚሰጣት አራተኛዋ ከተማ መሆኗን አንስተዋል፡፡ ምንም እንኳን ከተማዋ በዓለም ቅርስነት የተመዘገበች ቢሆንም በአፍሪካ እና በመላው ዓለም ሙስሊም ማኅበረሰብ ዘንድ መታወቅ ባለባት ልክ እንዳልታወቀችም ያስረዳሉ፡፡

በመሆኑም በመላው ዓለም ለሚገኙ ሙስሊሞች የሐረርን ባሕላዊ እና ማኅበራዊ ትስስር ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ ማስተዋወቅ እንደሚገባ አብራርተዋል፡፡ ለዚህም በያዝነው ዓመት በዩኒስኮ የማይዳሰስ የዓለም ቅርስ ዝርዝር ውስጥ የሰፈረውን የሸዋል ኢድ እና ሌሎች ቅርሶች እንደ መልካም እድል መጠቀም ያስፈልጋል የሚል ምክረ ሀሳብ ይሰጣሉ።

### እንደ መውጫ

ኢትዮጵያ ከእስልምና ሀይማኖት ጋር በተያያዘ በርካታ የመስህብ ሀብቶች ባለቤት ብትሆንም በሚፈለገው መጠን ጎብኚዎችን መሳብ እንዳልቻለች በተደጋጋሚ ይነሳል። ከእስላማዊ ቅርሶች ባሻገር በሌሎች የመስህብ ሀብቶች ላይም ተመሳሳይ ነገር ይስተዋላል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን መንግስት የቱሪዝም ዘርፉን ከዋንኛ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ውስጥ አንዱ በማድረግ፣ ታላላቅ የመዳረሻ ልማት ስራዎችን በማከናወን ስር ነቀል የሚባል ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀምሯል።

ከእነዚህ እርምጃዎች ውስጥ አንዱ ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው ገብተው ታሪክ፣ ባህል፣ ሃይማኖትና ማንነታቸውን የሚያንፀባርቁ የመስህብ ሀብቶችን እንዲጎበኙ፣ ከዚያም ባሻገር ለቀሪው ዓለም እንዲያስተዋውቁ የሚያስችል ንቅናቄ መፍጠር ነው። ባለፉት ዓመታትም ሀይማኖታዊ በዓላትን ተከትሎ ተደጋጋሚ ጥሪዎችን በማድረግ ውጤት መታየት መጀመሩን መረጃዎች ያሳያሉ። በምሳሌነትም የረመዳንና ሌሎች መሰል በዓላትን በማስመልከት የሁለተኛው ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ዲያስፖራዎች ወደ አገራቸው መግባታቸው ይታወቃል። ይህ ጅምር እስላማዊ ቅርሶች እና መስህቦች ይበልጥ እንዲተዋወቁና ትኩረት እንዲያገኙ መንገድ እንደሚከፍት ይጠበቃል።

ምህዳሩ ቢመቻች በመላው ዓለም የሚገኙ የሀይማኖቱ ተከታዮችም ሆኑ ሌሎች ጎብኚዎች ስለ ኢትዮጵያ ኢስላማዊ ቅርሶች ይበልጥ ማወቅ እንደሚሹ ጥርጥር የለውም፡፡ ይህን በማድረግ የሀገሪቷን የቱሪዝም ዘርፍ በሌላ ተጨማሪ አቅጣጫ ማሳደግ እንደሚቻልም እንደ ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ ያሉ ምሁራን በተደጋጋሚ ሲያስገነዝቡ ይደመጣል። ይህንን ምክረ ሀሳብ የሚመለከተው ባለድርሻ አካል ተግባራዊ እንደሚያደርገው ይጠበቃል።

ጎብኚዎችን ትኩረት ያደረጉ ልዩ መርሀ ግብሮች በማዘጋጀት የቱሪዝሙን ዘርፍ የበለጠ ማነቃቃት እንደሚቻል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባየናቸው ምሳሌዎች ማረጋገጥ እንችላለን፡፡ አፍሪካውያን በኢትዮጵያ ስላሉት ኢስላማዊ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ስፍራዎች የበለጠ እንዲያውቁ በማድረግ በኩል መንግስት እና ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መላው ዓለምም ኢትዮጵያ ሙስሊምና ክርስቲያኑ አብሮ ባህሉን እና ሃይማኖቱን የሚያከብርበት ሀገር መሆኑን እንዲገነዘብ ተከታታይ የማስተዋወቅ ስራዎች ሊተገበሩ ይገባል፡፡

# ሳምንቱን በታሪክ

## የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የባንክ ሥራ አስኪያጅ

**ዋሰልኝ አየለ**

የኢትዮጵያን የባንክ ዘርፍ የመሩት የመጀመሪያዎቹ የባንክ ስራ አስኪያጆች የውጭ አገራት ዜጎች ነበሩ። ‹‹ኢትዮጵያውያን ለባንክ ስራ አመራር ብቁ አይደሉም›› የሚለውን አስተሳሰብ በመስበር አመራሩን ከእነዚህ ዜጎች ተረክቦ ዘርፉን ውጤታማ ማድረግ ቀላል አልነበረም። በዚህ ከፍተኛ ጥረትና ጥበብ በሚጠይቅ መንገድ ተጉዘው ዘርፉን ውጤታማ ካደረጉት ፊር ቀዳጅ ኢትዮጵያውያን መካከል ተፈራ ደግፌ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ባለሙያ ናቸው። በስማቸው የባንክ ቅርንጫፎች ሁሉ የተሰየሙላቸው እኚህ ጀግና የዚህ ሳምንት ክስተት ስለሆኑ ታሪካቸውን ዘርዘር አድርገን እናያለን። ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን አጠር አጠር አድርገን እናስታውስ።

ከ96 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሰኔ 7 ቀን 1920 ዓ.ም (በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር ጁን 14 ቀን 1928) ዓለም አቀፉ አብዮተኛ፣ አርጀንቲናዊው የማርክሲስት አቀንቃኝ፣ የነፃነት ታጋይ፣ ሐኪም፣ ደራሲ፣ መምህር፣ ዲፕሎማት፣ የወታደራዊ ሳይንስ ባለሙያ እና የጦር መሪ ... ኧርኔስቶ ‹‹ቼ›› ጉቬራ ተወለደ። ይህ ዘርፈ ብዙ ባለሙያ በዋነነት በማርክሲስት አብዮተኛነቱ ይታወቃል። ለሌሎች ዓለም አቀፍ አብዮቶችም አርዓያ ተደርጓል። በኢትዮጵያም በተለምዶ ‹‹ያ ትውልድ›› እየተባለ የሚጠራው የ1960ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ

**ፋኖ ተሰማራ**
**ፋኖ ተሰማራ**
**እንደ ሆቺ ሚኒ**
**እንደ ቼ ጉቬራ**

የሚል መሪ ቃል ነበረው። ይህ መፈክር ዛሬ ድረስ ያንን ትውልድ ለማስታወስ ጥቅም ላይ ሲውል ይሰማል።

ከ86 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሰኔ 7 ቀን 1930 ዓ.ም ጀግናው ዘርዓይ ደረስ በሮም አደባባይ የጣሊያንን ሕዝብ አፍ ያስያዘ የጀግንነት ታሪክ ፈጸመ። የኢጣሊያ መንግሥት የኢትዮጵያን ድንበር ጥሰው በመግባታቸው በዶጋሊ ጦርነት ዶግ አመድ ለሆኑት ጣሊያናውያን ሰኔ 7 ቀን 1930 ዓ.ም የመታሰቢያ መርሃ ግብር በሮም ከተማ በአንድ የመንግሥት አደባባይ ላይ አዘጋጅቶ ነበር። በዚህ ዝግጅት ላይ ነበር ጀግናው ዘርዓይ ድረስ ጣሊያኖችን በጎራዴ የጨፈጨፋቸው። የዚህን ጀግና ሙሉ ታሪክ ሰኔ 11 ቀን 2015 ዓ.ም የታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ማግኘት ይቻላል።

ከ42 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሰኔ 6 ቀን 1974 ዓ.ም ጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ተወለደ።

አሁን በዝርዝር ወደምናየው የባንክ ባለሙያው ተፈራ ደግፌ ታሪክ እንሂድ።

ተፈራ የተወለደው ሰኔ 8 ቀን 1918 ዓ.ም በቀድሞው የሸዋ ጠቅላይ ግዛት፣ አንኮበር አውራጃ፣ አንበሴ በሚባል ቀበሌ ነው። አባቱ አቶ ደግፌ በላይነህ፤ እናቱ ወይዘሮ እርገጫቸው ገብረማርያም ይባላሉ። እድሜው ሰባት ዓመት ሲሆን ለትምህርት ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከአክስቱ ወይዘሮ ጌጤ ገብረማርያም ዘንድ መኖር ጀመረ። ከአንድ ቄስ ዘንድ ፊደል ከቆጠረ በኋላ አሊያንስ ፍራንሲስ በሚባለው የፈረንሳይኛ ትምህርት ቤት ገብቶ ዘመናዊ ትምህርት መማር ጀመረ።

ለሁለት ዓመታት ያህል እንደተማረ በ1928 ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን በመውረሩ ትምህርት ቤቱ ተዘጋ፤ ተፈራም ትምህርቱን አቋረጠ። ተፈራ በአምስት ዓመቱ የፋሺስት ኢጣሊያ የወረራ ዘመን የኖረው ሌቭድሮዝደቭስኪ ከተባሉ የሩስያ ዜጋ ጋር ነበር። በጊዜውም ታዳጊው ተፈራ የሰውየው ረዳት ሆኖ አገልግሏል። ከሰውየው ልጅ ጋር በመማርም የሩስያና የጣሊያንኛ ቋንቋዎችን አወቀ። በእነዚህ ቋንቋዎችም ብዙ መጽሐፍትን ማንበብ ቻለ።

በ1933 ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ከኢትዮጵያ ሲባረር የተፈራ ረዳት የነበሩት የውጭ አገር ዜጎች ከኢትዮጵያ ስለወጡ ታዳጊው ተፈራ ከባድ የሕይወት ፈተና አጋጠመው። የትምህርት ዕድል ባለማግኘቱ በአንድ የስፌት መኪና ኩባንያ ውስጥ በአስተርጓሚነት ተቀጠረ። በኩባንያው ውስጥ ለአንድ ዓመት ያህል ከሰራ በኋላ የመማር ጉጉት ስለነበረው ሥራውን ለመተው ወሰነ።

እንዳጋጣሚ ሆኖ አዲስ የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ቋንቋ የሚያውቁ ሠራተኞች እየፈለገ ይቀጥራል መባሉን ሰምቶ ማመልከቻውን በፈረንሳይኛ ቋንቋ አቀረበ። የባንኩ ስራ አስኪያጅም ተፈራ እንዲቀጠር ፈቀዱ። በ1936 ዓ.ም በ18 ዓመቱ በኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ በጸሐፊነት ተቀጠረ። ስራውን ለማከናወን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ አስፈላጊ ስለነበር ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ‹‹ብሪቲሽ ኢንስቲትዩት›› በተባለው ተቋም እንግሊዝኛ ለመማር ተመዘገቡ። በባንኩ ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ከሠራ በኋላ ከሌሎች ወጣት ሠራተኞች ጋር ተመርጦ ትምህርቱን ለማሻሻል ኮተቤ ወደሚገኘው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተላከ። ለአንድ ዓመት ተምሮ በ1938 ዓ.ም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ካናዳ ተላከ። ይህም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ካናዳ ከተላኩት የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች መካከል አንዱ ያደርገዋል።

ካናዳ እንደደረሰም መጀመሪያ ያመራው ካልጋሪ፣ አልበርታ ወደሚገኘው የንግድ ኮሌጅ ነበር። በአንድ ዓመት ውስጥ ትምህርቱን ጨርሶ በዲፕሎማ ተመረቀ። ወዲያውኑም የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን ለመቀጠል ብሪቲሽ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ገባ። ኮሜርስ ፋኩሊቲ በየዓመቱ የበጋ ትምህርት ጭምር እየወሰደ በ1942 ዓ.ም በዲግሪ ተመረቀ። ለተጨማሪ ሁለት ዓመታት የሕግ ትምህርት ተከታትሎ በ1945 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ የባንክ አገልግሎቱን ቀጠለ።


እነ ተፈራ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ባንኩ አድጎ፤ የሰራተኛው ቁጥርም ጨምሮ ነበር። ሌሎች ሰራተኞችም ትምህርትና የባንክ ስራ ስልጠና እንዲያገኙ እነ ተፈራ ማሳሰብ ጀመሩ። ሠራተኛው በየደረጃው የማታ ትምህርት እንዲከታተል ታስቦ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በባንኩ እርዳታ የማታ ትምህርት የሚያስተምሩ ምሁራን ተቀጠሩ። የባንክ ሠራተኞች ትምህርት ከጀመሩ በኋላ ከሌሎችም መንግሥታዊ ድርጅቶች ብዙ የማታ ተማሪዎች ተመዘገቡ። የዩኒቨርሲቲው ትምህርት ሊደራጅ የቻለው በባንክ ድጋፍ የተጀመረው ትምህርት ተስፋፍቶ ነው።

የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተወግዶ ነጻነት ከተመለሰ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደገና በመቋቋም ላይ ሳለ ኢትዮጵያ የራሷን ባንክ ለማቋቋም ስትነሳ ብዙ ችግሮች አጋጥመዋት ነበር። እንግሊዝ በወቅቱ በኢትዮጵያ የነበረውን የባንክና የገንዘብ ስርጭት ከምስራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶቿ ጋር አቀላቅላ የማስተዳደር ፍላጎት ነበራት። ሆኖም ችግሩን በውስጥ ምክርና ድፍረት በማለፍ በ1934 ዓ.ም ‹‹የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ›› በአዋጅ እንዲቋቋም ተደረገ።

በጦርነቱ ጊዜ የታላቋ ብሪታኒያን የጦር ሠራዊት ተከትሎ መጥቶ የኢጣሊያ ባንኮችን አስወግዶ የባንኩን ሥራ ተረክቦ የሚያስተዳድረው ባርክሌይስ ባንክ ነበር። ‹‹የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ›› ይህንን የእንግሊዝ ባንክ ተክቶ ነው ሥራውን የጀመረው። ባንኩ የተዋቀረው የጠቅላይ (ማዕከላዊ) ባንክንና የንግድ ባንክን ሥራ አጣምሮ እንዲሠራ ነው። ባንኩ ሥራውን ሲጀምር የነበሩት አብዛኞቹ ሠራተኞች የውጪ አገራት ዜጎች ነበሩ። ብዙዎቹ ከኢጣሊያ ወረራ በፊት የነበረው የቀድሞው የኢትዮጵያ ባንክ ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩ ናቸው።

ሰራተኛው እርስ በእርስ እየተረዳዳ ይማማር ነበር፤ የባንኩ ስራ እየተስፋፋ ሲሄድ የገጠር ቅርንጫፎች መከፈት ጀመሩ። የእነዚህ ቅርንጫፎች ኃላፊዎችም የውጭ አገራት ዜጎች ነበሩ። በ1937 ዓ.ም አዲስ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአሜሪካ በምስጢር ተዘጋጅቶ ታውጆ ወጣ። በዚህም የኢጣሊያ ሊሬ እና የምስራቅ አፍሪካ ሺሊንግ በአዲሱ የኢትዮጵያ ብር ተለወጠ። የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክም የባንክ ሥራው ቀስ በቀስ እየሰመረለት ሄደ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ እንደ ንግድ ባንክ ሆኖ ሲሠራ መጀመሪያ የሚሰጠው አገልግሎት የተንቀሳቃሽ ሂሳብና የገንዘብ ማስተላለፍ ሥራ ነበር። ሥራው እየደረጀ ሲሄድ ተደራቢ ሥልጣን ተሰጠው። በ1938 ዓ.ም የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎት መስጠት ጀመረ። የባንኩን ሥራ ለሕዝቡ ለማለማመድና በባንኩ እምነትን ለመፍጠር ብዙ ዓመታትን ፈጅቷል። ባንኩ በሰራተኞቹ ትጋትና በመንግሥት ድጋፍ ሁለገብ ድርጅት ሆኖ ጠቅላላ የባንክ አገልግሎትን ማስፋፋቱን ቀጠለ። ዘመናዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሲጀመርና ትምህርትም እየተስፋፋ ሲሄድ ኢትዮጵያውያን ሥራውን እየተላመዱ፣ የባንኩን የአመራር ሥራም እስከመያዝ በቁ። በእነዚህ ሁሉ ሂደቶች ውስጥ የነ ተፈራ ጥረትና አበርክቶ ከፍተኛ ነበር።



አቶ ተፈራ ደግፌ

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ በውጭ አገራት የሚሠሩ ሁለት ቅርንጫፎች ነበሩት። የመጀመሪያው የትራንዚት ሥራ የሚሠራ የጂቡቲ ቅርንጫፍ ነበር። ሁለተኛው ለባንክ አገልግሎት ሱዳን ውስጥ የተቋቋመው የካርቱም ቅርንጫፍ ነበር። እ.ኤ.አ በ1957 የወቅቱ የንግድና ኢንዱስትሪ ምክትል ሚንስትር በነበሩት አቶ ጌታሁን ተሰማ የሚመራ የንግድ ልዑካን ቡድን ወደ ሱዳን ሲሄድ ተፈራ የቡድኑ አባል ሆኖ ሄደ። የቡድኑ ጉዞ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የነበረው ንግድ የሚዳብርበትን እቅድ ለማጥናትና የንግድ ውል ለመደራደር ነበር። ለዚህ ዓላማ ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ቅርንጫፍ በካርቱም ቢከፈት ለሁለቱ አገሮች የጋራ ንግድ እንደሚረዳ ታምኖበት ጥያቄው ቀረበ። የሱዳን መንግሥትም የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ቅርንጫፍ በካርቱም እንዲቋቋም ፈቀደ።

የንግድ ልዑካኑ ሪፖርት ቀርቦ ከተፈቀደ በኋላ ለታቀደው የባንክ ቅርንጫፍ ብቁ የሆነ ሥራ አስኪያጅ በአስቸኳይ ተመርጦ እንዲቀጠር ባንኩ ታዘዘ። በወቅቱ የባንኩ ገዥ የነበሩት አሜሪካዊ ጆርጅ ሬይ ‹‹በሥራው የሰለጠነ ኢትዮጵያዊ የለም›› በማለት የአንድ እንግሊዛዊ ዜጋ ስም አቀረቡ። ይሁን እንጂ ‹‹ለታቀደው ዓላማ የውጭ ዜጋ አይበጅም›› ተብሎ የባንኩ ምርጫ ውድቅ ሆነ።

በዚያን ጊዜ አቶ ተፈራ ደግፌ የሲቪል አቪዬሽን ዋና ዳይሬክተር ሆኖ ይሰራ ነበር። አቶ ተፈራ የባንኩን የካርቱም ቅርንጫፍ እንዲመሩ የቅርንጫፉ ሥራ አስኪያጅ ሆነው በጽሕፈት ሚኒስቴር ማዘዣ ተሾሙ። ከምክትል ሥራ አስኪያጁ ከአቶ ከበደ ሠረቀብርሃን ጋር ሆነው ቅርንጫፉን ለማቋቋም ወደ ሱዳን ሄዱ። ከዋናው መሥሪያ ቤት አራት ኢትዮጵያውያን ኃላፊዎች ተመርጠው ተልከው በ1950 ዓ.ም የባንኩ የካርቱም ቅርንጫፍ ተከፈተ። ለቅርንጫፉ የሚስማሙ ሱዳናውያን እየተመለመሉ እንዲሰለጥኑና እንዲቀጠሩ ተደረገ። በተቻለ መጠን የባንኩ ገጽታ አፍሪካዊ እንዲሆንም ጥረት ተደርጓል። ቅርንጫፉ በአጭር ጊዜ ብዙ ደንበኞችን አፍርቶ ተወዳጅ ሆነ። የባንኩ ሙሉ ስም ለአረብኛ ተናጋሪዎች ስለሚያስቸግር የባንኩ ደንበኞች ቅርንጫፉን በወዳጃዊ አጠራር ‹‹ባንክ ኤል ሐበሺ›› ብለው ሰየሙት።

በወቅቱ ሱዳን ውስጥ ስድስት የውጭ አገራት ባንኮች ነበሩ። ከእነዚህ መካከል ብቸኛው አፍሪካዊ ባንክ ደግሞ የኢትዮጵያው (የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የካርቱም ቅርንጫፍ) ነበር። በአቶ ተፈራ ደግፌ ይመራ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የካርቱም ቅርንጫፍ ከደረጁ የምዕራባውያንና የአረብ አገራት ባንኮች ጋር ተወዳድሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ደንበኞች ማፍራትና አትራፊ ለመሆን በቃ። ይህም ቅርንጫፉ ለኢትዮጵያ የባንክ ዘርፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት አስችሎታል።

የካርቱሙ ቅርንጫፍ ለአስር ዓመታት ያህል ካገለገለ በኋላ በጄኔራል ኒሜሪ ዘመነ መንግሥት እ.ኤ.አ በ1969 የግል ባንኮች ሁሉ በሱዳን መንግሥት ሲወረሱ አብሮ ተወረሰ። በ1960 እና በ1970ዎቹ በአገር ውስጥ ለባንክ አመራር ብቁ ሆነው ያገለገሉት አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን የባንክ ባለሞያዎችና ኃላፊዎች ካርቱም ቅርንጫፍ እየሠሩ በቂ ልምድ ያገኙ ናቸው። ለአብነት ያህልም አቶ ከበደ ሠረቀብርሃን፣ አቶ መስፍን በለጠ፣ አቶ ታደሰ አበበ፣ አቶ ስሜ ታከለ፣ አቶ ቸርነት በየነ፣ አቶ ተሳለ ወርቁ፣ አቶ ጌታቸው ደስታ እና ወይዘሮ በላይነሽ ማንደፍሮ ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች ታዋቂ የባንክ ባለሙያዎች ሆነው እያንዳንዳቸው በብሔራዊ ባንክና በንግድ ባንክ ውስጥ ከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ ላይ መድረስ ችለዋል።

እስከ 1953 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ገዢዎች የውጭ አገራት ዜጎች ነበሩ። ኢትዮጵያውያን በከፊል ስልጣን መጋራት የጀመሩት አቶ የወንድ ወሰን መንገሻ እ.ኤ.አ በ1959 ዓ.ም የባንኩ ምክትል ገዥ ሆነው ሲሾሙ ነው። በ1953 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ደግሞ አቶ ተፈራ ደግፌ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሾሙ። ይህ የአቶ ተፈራ ሹመት ‹‹ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክን ለመምራት ብቁ አይደሉም፤›› የሚለውን አስተሳሰብ ውድቅ ያደረገና ከ1937 እስከ 1952 ዓ.ም ድረስ በስድስት የውጭ አገራት ዜጐች ሲተዳደር የቆየው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክን በኢትዮጵያዊ ስራ አስኪያጅ መመራት መጀመሩን ያበሰረ የለውጥ እርምጃ ሆኖ በታሪክ ተመዝግቧል።

ከዚያ በኋላ ከዚያ ቀደም ያልታየና ከፍተኛ የሆነ የብድር እድገት፣ የቅርንጫፎች መስፋፋትና የገቢ መጨመር ተመዘገበ።

የተሟላ የባንክ አገልግሎት በአዲስ መልክ ለማቋቋም እቅድ ወጣ። ይህ የባንክን አቋም የማሻሻል እቅድ ሰፊ ጥናት እንደሚያስፈልገው ታውቆ ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት አንድ ባለሙያ በመቅጠርና ጥናት በማስጠናት አዲስ የባንክ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለፓርላማ ቀረበ። በአዋጁ መሰረት የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ለሁለት ተከፍሎ አንዱ ማዕከላዊ (ብሔራዊ) ባንክ፤ ሌላው ደግሞ የንግድ ባንክ ሆነው እንዲቋቋሙ ተወሰነ።

በታህሳሥ 1956 ዓ.ም ሁለቱ ባንኮች (የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ) ተደራጅተው ስራቸውን ጀመሩ። አቶ ምናሴ ለማ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ፤ አቶ ተፈራ ደግፌ ደግሞ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሾሙ። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ1960ዎቹ ከፍተኛ እድገት ሲያስመዘግብ አቶ ተፈራ በዋና ስራ አስኪያጅነት ይመሩት የነበረውና በ20 ሚሊዮን ብር መነሻ ካፒታል የተቋቋመው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አስተዋፅዖው ከፍተኛ ነበር።

ባንኩ በአዲስ መልክ ሥራውን እንደጀመረ ዋና እቅዱ ሠራተኞቹን ማሰልጠንና የባንክ ቅርንጫፎቹን ማስፋፋት ነበር። የባንክ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል በመክፈት የሰራተኞቹን አቅም ለማሳደግ ሰፊ ጥረት አድርጓል። በዚህም ባንኩ ጥሩ አፈፃፀም እንዲኖረው ማድረግ ተችሏል። ሌሎች የገንዘብና የመድን ተቋማት ያለባቸውን የሰው ኃይል እጥረት ለማቃለልም ሚናው የጎላ ነበር። ለዚህ ሁሉ የአቶ ተፈራ ደግሜ ሚና ከፍተኛ ነበር።

በእርሳቸው ፋና ወጊነት የተጀመረው የኢትዮጵያውያን የባንክ መሪነትም እስካሁን ድረስ ተጠናክሮ ዘልቋል። ከ1966 እስከ 1968 ዓ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዋና ገዥ በመሆን አገልግለዋል።

ወታደራዊው መንግሥት ስልጣን በያዘ ማግሥት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተወርሶ በብሔራዊ ባንክ ስር ሆነ። አቶ ተፈራም ‹‹ለአብዮቱ እንቅፋት እንዳትሆን›› ተብለው ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ለሰባት ዓመታት ያህል ለእስራት ተዳረጉ። ከእስራት ከተፈቱ በኋላም ኑሯቸውን በተማሩባት ካናዳ አድርገው ቆይተዋል። በዚምባብዌና በስዋዚላንድ የባንክ አማካሪ ሆነውም ሰርተዋል። የተማሩበት ብሪቲሽ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲም የሕግ የክብር ዶክትሬት ሰጥቷቸዋል። በአዲስ አበባ የሚገኘው መኖሪያ ቤታቸውን ለአዲስ አበባ የፌስቱላ ሆስፒታል በስጦታ ያበረከቱት አቶ ተፈራ፤ ከካናዳዊት ባለቤታቸው ሁለት ልጆችን አፍርተዋል። አንጋፋው ባለሙያ በስራቸው ላበረከቷቸው አስተዋፅዖዎች በርካታ ሽልማቶችን አግኝተዋል። የምርምር መጻሕፍትንም ጽፈዋል።

የኢትዮጵያን የባንክ ስርዓት እንዲዘምን ካደረጉት ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት አቶ ተፈራ ደግፌ የካቲት 27 ቀን 2007 ዓ.ም አርፈው ስርዓተ ቀብራቸው በቫንኩቨር ካናዳ ተፈፅሟል።

# የዝነኞች ገጽ

## ጦቢያው የጥበብ ሁዳዴ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ለጥበብ ቤት ሰደቃ ሆነው ለኪነ ጥበብ ቤዛ ከሆኑ የመድረክ ጦቢያዎች መሀከል አብራር አብዶን ሳንጠቅስ ማለፍ አንችልም። አብራር አብዶ ካሉማ...ከአዲስ አበባ ወልቂጤ፣ ከወልቂጤ ሆለታ...በፍቅር ተጸንሶ፣ በሸጋዎቹ ኢማን ተወልዶ፣ በአላህ ሂጅራ መንገድ ታንጾ፣ ከሀዲስ ቁርአን ቀርቶና በሥራ ባህል ተቀርጾ ሲያድግ፤ ለሕይወት ምስጢሩ የኑሮ ሀጃ የእርሱ የታላቅነት ዓቂቃው ፍቅር ብቻ ነው። ስለ ጦቢያው እያነሱ ስለ እርሱ ካወሩማ ሩብ ጨረቃ ጀሮዋን አንጠልጥላ፣ ዛፎቹም ቅጠላቸውን አዝምመው ቁልቁል እያንጋደዱ ልስማ ማለታቸው አይቀርም። በጀነት አፈር ላይ እንደወደቀች ፍሬ ሀድራው የጎመራ ነውና "የዝነኞች"ም ዝናውን ሊያወሳ ይወዳል።

በሀገራችን የቲያትር ፊልምና ሙዚቃ እንዲሁም በውዝዋዜ መድረኮች ላይ ምን ቀረሽ የማይባል ሁለገብ የጥበብ ማቶት፣ የጉብዝናው አፎት ስለመሆኑ አያጠራጥርም። ከሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ደጅ ብቅ ብላችሁ አብራር አብዶ ብትሉ እንኳንስ ሰውና የግቢው ዛፍ ተክሉም ስለ እርሱ ይነግራችኋል። በቲያትሩ ብቻ ከ67 በላይ በሆኑ ቲያትሮች ውስጥ ቀልብን በሚሰልበው የትወና ብቃቱ ታይቷል። ፊልሙን ማን ይቁጠረው...ያ የሚያስገመግመው ብራቅ ድምጹ እንኳንስ የሰውን የአንበሳን ቁጣ ያበርዳል። ውስጡ ገራገር ሆደ ቡቡ ነው። ሲፈልግ ግን የፈለገውን ሆኖ በመተወን እሳትም ውሀም መሆኑን ይችልበታል። በቲያትር መድረኮች ላይ ብቻም ሳይሆን በእንግድነት በሚቀርብባቸው መድረኮች ላይም ማስደመሙን አያቆምም። በብዙ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይ ተመልክተነዋል። እራሱን ለጥበብ ሰደቃ አድርጎ ሲቀርብ የእርሷም እዝነት ከችሮታው አልሰሰተችበትም። ደግሞ ውዝዋዜውም የግሉ ነው። በሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ለረዥም ዘመናት በባህላዊ ውዝዋዜ ሲያሰለጥን ቆይቷል። በእንቅስቃሴያዊ የጥበብ ስልት፤ በኬሮግራፊውም ክህሎቱ የዳበረ ነው። ሁልጊዜም ባይሆን ከነሸጠው ግን በግጥምና ዜማውም ዓልሞ ተኳሽ ነው።

የዓባይ ዳር እንኮይ፣ የሙዚቃውን መዲና ማህሙድ አህሙድን ከሁሉም በፊት ቀርቦ ከጅረት ቅላጼው ፏፏቴ ውስጥ የተስፋ እርስቅነቱን ተመልክቷል። "አልሙ ሌሌ" ማህሙድ ከመነሻው እጅግ የተወደደባት የጉራጊኛ ሙዚቃ ናት። ይህችን ሙዚቃ ግጥምና ዜማዋን ሠርቶ፣ በካሴትም አስቀድቶ እንዲያጠናት የሰጠው አብራር አብዶ ነበር። ፒያሳ ማሕሙድ ሰፈር "ሳባው" ሙዚቃ ቤት እየተመላለሱ አብራርም ማሕሙድን ያስጠናዋል። ተሠርቶም በካሴት ወጣ። ሙዚቃው እጅግ ተወደደና ገጠር ከተማውን አጥለቀለቀው። ታላላቆች በሕይወታቸው ውስጥ የሚሠሩት ሌላ አንድ ታላቅ ሰው ይኖራል። የአብራር አብዶ የታላቅነት ጀማ ፍሬው እንዲህ ከራሱ አልፎ በሌሎቹም ላይ የተንዠረገገም ጭምር ነው። በውብ ቀለማት ያሸበረቀው ኢትዮጵያዊ ጉራጌነትና የፍቅር ሁዳዴ ኢትዮጵያዊ እስላማዊነት ማደሪያቸው የእርሱ ልብ ነው። የጥበብን ኩታ ለብሶ ከመድረክ ላይ ሲቆም የጥበብ ጥላው በጣራ ግርግዳው ላይ ሁሉ ስዕል ሠርቶ ይታያል። በሀይማኖታዊ ቦታና ጊዜ ሸርጡን አሸርጦ በዱአና በሶላቱ ቀናኢ መንፈሳዊነቱ ከልቡ አልፎ ከፊቱ ላይ ይረብባል። ከአንዱም ሳያጎድልና ሳይጎድል፣ ከሁሉም ሁሉንም እርስቁ ያደረገ ግሩም ኢትዮጵያዊ የጥበብ ልጅ ነው። የእርሱ መታወቂያ ሕዝባዊ ሀገር ወዳድነትና ባህል ሀይማኖቱን አክባሪነቱ ነው። ሕብራዊ ልቦናው የሁሉንም ብሔር ቋንቋ ባህል ወግና እሴት ለማወቅ ሁሌም ያኮበኩባል። በበጎ አድራጎት ሥራዎች ውስጥም ከፊት ከምናሰልፋቸው የጥበብ ሰዎች መካከል አንዱ እርሱ ነው።

የሰው መውደድን ይስጥህ ብለው ከመረቁ አይቀር እንደ አብራር አብዶ ማለት ነው አንጂ...ማንም ስሙን በክፉ አያነሳውም። ለኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ስላበረከተው ትልቅ አበርክቶ በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚኖር ኢትዮጵያዊ የሚመሰክረለት ሰው ነው። በ2007 ዓ.ም በፍራንክፈርት ከተማ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከአንድ የጥበብ አዳራሽ ውስጥ ሰብሰብ ብለዋል። ምክንያቱ ደግሞ በዚያ የሚገኘው "የኢትዮጵያ ብሔራዊ የኪነ ጥበብ ማዕከል" ለሀገር ባለውለታ የኪነ ጥበብ ልፋተኞች እውቅናና ሽልማት ሊያበረክት መሆኑ ነው። በዕለቱ አብራር አብዶም ከዚያው ተገኝቷል። በዝግጅቱ መሀል ግን ከመድረኩ ላይ ወጣ። "ጴጥሮስ ያቺን ሰዓት" የተሰኘችውን የሎሬት



አብራር አብዶ

ጸጋዬ ገ/መድህንን ድንቅ ተውኔት መተወን ጀመረ። አብራር ያቺን ሰዓት ፈጽሞ አብራርን አነበረም። ሎሬቱ እርሱን እየተመለከተ የጻፈው ይመስላል። አቤት የትወና ብቃት! አብራር ያቺን ሰዓት ተመልካቹን ሁሉ ቁጭ ብድግ አደረገ። በዕለቱም በኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ውስጥ ለ42 ዓመታት ያህል ላበረከተው የጎላ ሚና የክብር ሽልማትና ዕውቅና አበረከቱለት።

ሀገር ፍቅርና አብራር አብዶ ውሀና ጀልባ እንደማለት ናቸው። ጀልባ ያለውሀ ባዶ ገንዳ ብቻ ነው። ለአብራር የቅርቡ የሆኑት ድንገት እርሱን ከቤት ከሰፈሩ ፈልገው ያጡት እንደሆነ የት ሊገኝ እንደሚችል ያውቁታል። የሕይወቱ ጀልባ ያለ ሀገር ፍቅር አትቀዝፍም። በግቢና በዙሪያዋ ተገኝቶ አየሯን ካልማገ በስተቀር ሳንባው ሌላ አየር የሚቀበል መስሎ አይሰማውም። ነዳጅ ጨርሳ ወደ ማደያ እንደምትሮጥ መኪና እርሱም ወደ ሀገር ፍቅር ይገሰግሳል። ማሕሙድ ጋር ቅጠሪኝን እንደሚወደው እንደ ጥንቱ አራዳ ፍቅር እርሱም ቀጠሮው ሁሉ ሀገር ፍቅር ቲያትር ነው። ለጨዋታ ቁም ነገሩ ሁሉ ከወዳጆቹ ጋር ለመቀጣጠር ደስ የሚለው ከዚያ ሲሆን ብቻ ነው። "ሀገር ፍቅር ከእናቴ በላይ የኖርኩባት ቤቴ ናት። እዛ ባልቀጥራቸውና ከሌላ ቦታ ቢሆን እንኳን ታክሲ ይዤ መጀመሪያ የምሄደው ወደ ሀገር ፍቅር ነው። እዚያ ሳልደርስ ሌላ ቦታ መሄድ አልችልም። ሁሉም ነገር ይጠፋብኛል። በመኪናዬ ሆኜ እንኳን ይዛኝ የምትሄደው ወደዚያ ነው። በሀገር ፍቅር ጀምሬ የጨረስኩትም በሀገር ፍቅር ነው።" በማለት በየአጋጣሚው ሁሉ ከቲያትር ቤቱ ጋር ስላለው ተጋምዶ በሀሴት ይናገረዋል። አብራር ኪነ ጥበብን በሀገር ፍቅር ከተዋወቃት ጀምሮ ጡረታ ለመውጣት ጥቂት ዓመታት ብቻ እስኪቀሩት ድረስ ከዚያ ወደየትም ውልፍት ብሎ አያውቅም። 57 ዓመት ሲሞላው በአንድ የግል ጉዳይ ሳቢያ ቀደም ብሎ ከሥራው ለቀቀ። ሥራውን እንጂ ሀገር ፍቅርን ግን ሊለቃት አልቻለም፤ በተቻለው መጠን ሁሉ ወደዚያው ለማቅናት ይቸኩላል። የሚገርመው ደግሞ ገና በጠዋቱ መደበኛ ሠራተኞች እንኳን ሳይገቡ ቀድሟቸው ከስፍራው የሚገኝ መሆኑ ነው። ሀገር ፍቅር የጥበብ ጡቷን ያጠባችው እናቱ፣ ያለእርሷ የማይታየው ሱሱ ናት።

ጊዜው 1970ዓ.ም፤ ወቅቱም የአብዮታዊው የቀይ ሽብር መጋረጃ ተገልጦ ቲያትር መሳይ ገሀዶች የሚታዩበት ነበር። በዚያን ጊዜ አብራር በሀገር ፍቅር ቲያትር ይሠራ ነበር። በዚያን ሰሞንም አንዱ የመንግሥት ካድሬ ከመሬት ተነስቶ እርሱንና አራት ባልደረቦቹን ጥምድ አድርጎ ያዛቸው። የጎሪጥ እያየ በልቡ ያሴርባቸው ጀመረ። ከዕለታት በአንዱ ቀን ግን የውሸት ካባውን ደርቦና የጠነሰሰውን በኪሱ ሸጉጦ አምስቱንም አስቀፈደዳቸው። እህ...ሲባል "ሀገር ፍቅርን ሊያፈርሱ አሲረው የተነሱ ናቸው" አለ። የውሸት ተንኮል ካባውንም አውልቆ ደረበባቸው። ነገሩ ግን ሳይሳካላት ቀረ። ለሁለት ቀን ያህል ብቻ ታስረው በነጻ ተለቀቁ።

በጡረታ እስከተገለለበት ቀን ድረስ የሠራቸውን ቲያትሮችም ሆኑ ፊልሞች ጠቅሰን የምንደርስበት አይደለም። ከሀገር ውስጥ አማርኛ ኦሮሚኛና ጉራጊኛ እንዲሁም ደግሞ ከውጭ ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዘኛና አረብኛ ቋንቋዎችን አቀላጥፎ መናገር የሚችለው አብራር አብዶ ጣሊያንኛን ግን አይችላትም። ታዲያ በአንድ የቲያትር መድረክ ላይ ጣሊያናዊ ሆኖ ጣሊያንኛን ከተንጋደዱ የአማርኛ ቃላት ጋር ቀይጦ ሲናገር ተመልክተነው ይሆን...ትወናው ብቻም ሳይሆን ሜካፕ ከተጨመረበት መልኩ ጋር ተደማምሮ ባራቴሪን መሰለ። "የምርም ጣሊያናዊ መስያቸው ከመድረክ ሆኜ ሊጎዱኝ ሙከራ ያደረጉብኝ ሰዎች ነበሩ" በማለት ለበርካታ ጊዜያት ስለታየው ትዕይትና አጋጣሚው ያወሳል። "ጴጥሮስ ያቺን ሰዓት" አብራር እንደ አቡነ ጴጥሮስ መስቀሉን ከአንገቱ አጥልቆ፣ ቆቡን ደፍቶ ሲተውን ተመልካቹን አስደምሞ በየመድረኩ አፍዝዟቸዋል። ከሰባት ዓመታት በፊት የጊዜው ምርጥ ፊልም ብለን ባጨበጨብንለት "ፍቅር ሲፈርድ" በተሰኘው ፊልም ውስጥ አብራር አይረሳም። ወጋየው ንጋቱ (ወጊሾ) ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዳይሬክት አድርጎ በተወነበት "ትዝብት" በሚለው ቲያትሩ ከአብራር ጋር አብረው ተውነውበታል። የዚያን ሰሞን ወጋየው ሕመሙ ጠንቶበት ነበርና ከዚህች ቲያትር በኋላ በመድረክ ሳይታይ በዚያው አሸለበ። ስለ ጦቢያው አብራር አብዶ ሥራዎች ካነሳን "ሌተር ፍሮም ዘ ሬድ ሲ" የሚታለፍ አይደለም። የትወና ችሎታው ባህር ተሻግሯል። የፊልሙ ታሪክ በአንድ ፈረንሳዊ ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን፤ መቼቱ ደግሞ በሐረርጌና በጅቡቲ ነበር። ሀገራችንን ጨምሮ በፈረንሳይ ቀኝ ግዛት ስር በነበሩ በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ለእይታ ቀርቧል። እንግዲህ እርሱ ያልጀመረውና ጀምሮም ያልጨረሰው የጥበብ ሁዳዴ የለም። በውዝዋዜ፣ ትወና አልፎም እስከ ግጥምና ዜማ ያልደረሰበት፤ ገብቶም ውሀ ያልጠጣበት ቤተ ጥበብ የት አለና...

አብራር አብዶና የመናዊቷ ሴት...በአንደኛው የወጣትነቱ ሰሞን እንዲህ ሆነ፤ አብራር በሚኖርበት ሰፈር ውስጥ ከምትኖር የመናዊት ኮረዳ ጋር ፍቅር ቢጤ ይጀምራል። ሁለቱም እፍ ጥብስ ከማለት አልፈው በፍቅር ክንፍ ወደማለት ገቡ። የትዳር ጎጆ ቀልሰው ከአንድ ጣራ በታች የፍቅር ቄጤማቸውን ለመቁረጥ አስመኛቸው። ድል ያለ ሠርግ ባይሆንም በትንሹ ለኒካ (ለቀለበት ሥነ ሥርዓት) የምትሆን ዝግጅት ማሰናዳት ጀመሩ። የተቆረጠው ቀን ደርሶም ከአባቷ ፊት ቆሙ። አባቷ ግን የሚገባውን ጥሎሽ ካልሰጣችሁ በስተቀር ልጄን አሳልፌ አልሰጥም አሉ። ምን ችግር አለው በማለት፤ ምን ያህል ነው የምንጥለው? ሲሉ ይጠይቃሉ። አባትም "40 ሺህ ብር" ይላሉ ቆፍጠን ብለው። ይኼኔ ነው መሸሸ...ሰውየው ሀሳባቸውን እንዲቀይሩ ወዲህ ቢሏቸው ወዲያ አሻፈረኝ እንዳሉ በአቋማቸው ጸኑ። በደስታ ልጃችሁን... ብለው ሄደው በተስፋ መቁረጥ እጃቸውን አጣምረው ተመለሱ። መካሪ አያሳጣን...ከፍቅሩ ነጥለው በ40 ሺህ ብር ያስቆዘሙትን አብራር፤ ከወዳጆቹ አንዲት ምክር ብልጭ ተደረገለት። "እርሷም ብትሆን ትወድሃለችና ጠልፈህ አግባት" ይሉታል። የጨነቀ ዕለት ሀረግም መንጠልጠያ ነውና በሀሳቡ ተስማማ።

አንድ ቀን አሳቻውን ጊዜ ጠብቀው በጓደኛው ቮልስዋገን መኪና ቱር! ብለው ከልጅቷ ሰፈር ደረሱ። ጠልፈውም ይዘዋት መጡ እሷም ትወደዋለችና በጠለፋው ተስማምታ ነበር። ተደፈርኩ ብለው የሚያስቡት አባቷ ከሄደች በኋላም አላስቆም አላስቀምጥ አሉት። አብራርና ባለቤቱ ግን በግፊያው እየተወተረተሩም ሦስት ልጆችን ወልደው ሳሙ። በኋላ ተስፋ የማይቆርጡት የአባቷ ንዝነዛ አየለና እሷም አመሏ ከፋ። ከፍቺ መልስ ሁለት ልጆች ለእሷ አንድ ልጅ ደግሞ ለሱ ተከፋፈሉ። ብዙም ሳትቆይ ጥላ ወደ የመን ሄደችና የቀሩትንም ልጆቹን አምጥቶ ለ15 ዓመታት ያህል እናትም አባትም እየሆነ ለብቻው አሳደጋቸው። ሁሉንም በትምህርት ቦታ ቦታ አሲዞም 1991 ዓ.ም ዳግም በትዳር ተጣመረ። ሁለተኛዋ ሚስቱ እሷም አንድ ልጅ ነበራትና በጋራ አንድ አክለው የአምስት ልጆች አባት ለመሆን በቃ። "ከልጆቼ በላይ አስበልጬ የምወደው ልጇ ነው" ይለዋል ባለቤቱ ከሌላ ስለወለደችው ልጅ ሲናገር። አሁን በአምስት ልጆችና በ8 ያህል የልጅ ልጆች ተከቦ አባትም አያትም ሆኗል።

አርቲስት አብራር አብዶ ባደገበት ቀዬውም ተወዳጅነትና ዝናን የተጎናጸፈ ምርጡና ፈርጡ የጉራጌ ልጅ ኢትዮጵያዊ ነው። እንደ ሀገር በታላላቅ የጥበብ መድረኮች ቆሞ ሲያስደምመን ተመልክተነዋል። ለባህሉ ያለው ውስጣዊ አክብሮት እጅግ የተለየ ነው። ታይቶ የማይጠገበውን ተልሶ የማይሰለቸውን የጉራጌን ባህል በማስተዋወቅ ግንባር ቀደም ከሆኑት መሀከል የሚታየው እርሱው እራሱ ነው። "የኋላው ከሌለ የለም የፊቱ" ነውና የትም እንሁን ከወዴት ዞረን የተነሳንበትን ማኅበረሰብ መመልከት ስንችል ያኔ ታላቅነታችን ይጎመራል። በአበርክቶዋቸን ከሁሉም ላሳደገን ማኅበረሰብ ብናደላ ውለታውን መለስን እንጂ ዘረኛ ሆንን ማለት አይደለም። አብራርን በተመለከተ ከጉራጌዎቹ መንደር ውስጥ አንድ መማር ያለብን ነገር ያለ ይመስለኛል። እነርሱ አክብረው ስለተቀበሉት እርሱም በሄደበትና በቀረበበት ሚዲያ ሁሉ ባህላቸውን አጉልቶ ያሳያል፤ ስለ እነርሱም ይጠየቃል ብዙ ጉዳዮችንም ያነሳል። ታዲያ እንደ ሀገር ሁላችንም ባለውለታዎቻችን አክብረን ብንቀበልና የሚገባቸውን ትኩረት ብንሰጣቸው ኖሮ እንዲሁ በዓለም ዓቀፍ ደረጃም ከሀገራቸው ጋር ከፍ ባሉ ነበር። ማኅበረሰቡን በተመለከተ በሚካሄድ በየትኛውም ኪነ ጥበባዊ ጉዳይ ቸል ብሎ አያውቅም። ለአብነትም በብሔራዊ ቲያትር በተዘጋጀውና በጉራጌ ማኅበረሰብ ውስጥ የሴቶች መብት ተሟጋች በሆነችው "የቃቄ ውርድወት" ትውፊታዊና ሙዚቃዊ ተውኔት ላይ ከተሳተፉ አንጋፋ የቲያትር ተዋንያን መሀከል አንዱ አብራር አብዶ ነው።

በኪነ ጥበቡም ሆነ በበጎ እንቅስቃሴዎቹ ለሚያደርገው ሁሉ ውለታውን እነርሱም ቢሆኑ አይዘነጉትም። በዚህ ብሩክ እንቅስቃሴው ላደረገላቸው ነገር ከፊቱ ቆመው በምስጋና ሸልመውታል። "አብራር..." ሲሉ በወልቂጤ ከተማ 2 መቶ ካሬ ሜትር መሬት እና 1 መቶ ሺህ ብር አበርክተውለታል። ከሁለት ዓመታት በፊትም ጉራጌዎቹ ባለውለታዎቻቸውን በሚሸልሙበት በ"ኬር" የእውቅናና የሽልማት ሥነ ሥርዓት በኪነ ጥበቡ ዘርፍ ላበረከተው አስተዋጽኦ እውቅና ሰጥተውታል። ገራገሮቹ ሲወዱት እኮ ወሰን የላቸውም። እንደ ኢትዮጵያዊ ባህላቸው፤ በየመድረኩ ጋቢውን እያለበሱ ያጌጡታል። እርሱም በአጸፋው ከፊታቸው ጎንበስ ብሎ ክብረቱን ፍቅር ባልተለየው ፈገግታ ያጎናጽፋቸዋል።

የቅርቦቹ የሆኑት ሁሉ በተጨዋወቱ ቁጥር የሚቀልዱበት አንድ ቀልድ አለ። የጉራጌ ልጅ መቼስ ሥራ ልማዱ አርማው ንግዱ ነውና "ለማንስ ብለህ ከኪነ ጥበብ ሥራ ጋር ትታሻለህ ለምን አትነግድም" ይሉታል። እርሱም በመልስ ምት "ጉራጌነቱ በዘር አንጂ በሙያ አይደለማ" ሲል ፈገግ ብሎ ይመልስላቸዋል።

ከፍቅራቸው የተቀዳው ፍቅር በሀገሩ የኪነ ጥበብ ደብር ታውሶ ያስታውሳቸዋል። አረፋን ከመስቀል እስልምናውን ከክርስትና በፍቅር አድባር አጣምረው በአንድነት ይመጅኑታል። አረፋውም በረካውን አስከትሎ መጥቷልና ይኼኔ እሱም ከዚያው ደርሷል። በዓመት አንዴ ልጅ ቢመጣ በአረፋው፤ መቼስ ከሕጻን ከአዛውንቱ "የተንቢ!...የተንቢ!" እንኳን በደህና መጣህ፤ ይምጣብኝ! ይምጣብኝ! "...ኔሁ! ኔሁ! አዶድ ከስ" እያሉ በናፍቆት ፌሽታ እየተቀባበሉ ግጥም አድርገው ሲስሙት... በእነርሱው ምርቃት "ኬር ይኹን አረፋ! ኬር ይኹን ኢትዮጵያ! ኬር ይኹን ጉራጌ!" ብዬ ላብቃ።

# ዓለም አቀፍ



## ሲሪል ራማፎሳ ለሁለተኛ ጊዜ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው ተሾሙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ለቀናት መንግሥት ለመመስረት በውዝግብ ውስጥ የቆየው የደቡብ አፍሪካ ፖለቲካ በመጨረሻም ሲሪል ራማፎሳን ለሁለተኛ ጊዜ የስልጣን ዘመን ፕሬዚዳንት አድርጎ ተጠናቋል።

የማንዴላ አፍሪካን ናሽናል ኮንግረስ ፓርቲ ከአፓርታይድ ማብቃት ከሦስት አስርት አመታት በኋላ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በ2024ቱ ምርጫ መንግሥት ለመመስረት የማያበቃውን ዝቅተኛ ድምጽ አግኝቷል።

ይህን ተከትሎ አጣማሪ መንግሥት ፍለጋ በምርጫው ከተሳተፉ የተለያዩ ፓርቲዎች ጋር ንግግር ሲያደርግ የሰነበተው ኤኤንሲ በነጭ ደቡብ አፍሪካውያን ከሚመራው ዴሞክራቲክ አሊያንስ ፓርቲ ጋር ለመጣመር ተስማምቷል።

ፓርላመንታዊ ሥርዓትን በምትከተለው ደቡብ አፍሪካ ፓርቲዎች ለምክር ቤቱ ወንበር ከተወዳደሩ በኋላ የምክር ቤት አባላቱ ፕሬዚዳንቱን ይሰይማሉ።

ሲሪል ራማፎሳ 400 መቀመጫዎች ባሉት ፓርላማ ከኢኤፍኤፍ ፓርቲ መሪው ጁሊየስ ማሌማ ጋር ለእጩነት የቀረቡ ሲሆን 283 የድጋፍ ደምጽ በማግኘት ለሁለተኛ ጊዜ ሀገራቸውን የመምራት እድል አግኝተዋል።

ፕሬዚዳንቱ በፓርላማው ምርጫ ከፓርቲያቸው ኤኤንሲ በተጨማሪ በ2024ቱ ምርጫ ሁለተኛውን ከፍተኛ ድምጽ ካገኘው ዴሞክራቲክ አሊያንስ ሰፊ ድጋፍን አግኝተዋል። እራሱን በፓን አፍሪካኒስትነት የሚገልጸው ጁልየስ ማሌማ ዝቅተኛ የተባለውን 44 ድጋፍ አግኝቷል።

ጥምር መንግሥት የመሰረቱት አፍሪካን ናሽናል ኮንግረስ እና ዴሞክራቲክ አሊያንስ ፓርቲ በርዕዮተ ዓለም እና በፖለቲካዊ አተያይ ፍጽም የተለያዩ ቢሆንም ደቡብ አፍሪካን በጋራ ለማስተዳደር ተስማምተዋል።

ተንታኞች የነጻነት ታጋይ በነበረው ኤኤንሲ እና በለዘብተኛው ዲኤ መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ መሆን ለራማፎሳ መንግሥት መጽናት አደጋ ሊሆን ይችላል ብለዋል።

ለአብነት ራማፎሳ በእስራኤል ጉዳይ ጠንካራ አቋም ይዘው በዓለም ወንጀለኞች ፍርድ ቤት ድረስ እንድትቀርብ እየጣሩ ቢሆንም አጣማሪው ፓርቲ ግን በዚህ ጉዳይ የተለየ አቋም ያለው ነው።

ራማፎሳ ፕሬዚዳንት ሆነው ከተመረጡ በኋላ ባደረጉት ንግግር “ይህ ለደቡብ አፍሪካ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ነው የተለያየ አቋም ቢኖረንም በደቡብ አፍሪካዊያን ደህንነት እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ዙሪያ ተቀራርበን እንሠራለን” ብለዋል።

## ቭላድሚር ፑቲን ከዩክሬን ጋር የተኩስ አቁም ስምምነት ለማድረግ ቅድመ ሁኔታ አስቀመጡ

በጋዜጣው ሪፖርተር



የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ከዩክሬን ጋር የተኩስ አቁም ስምምነት ከመደረሱ በፊት ዩክሬን ‘ከግዛቶቼ’ ወታደሮቿን ልታስወጣ ይገባል ሲሉ ቅድመ ሁኔታ አስቀመጡ።

ፕሬዚዳንት ቮሎዲሚር ዜሌንስኪ በበኩላቸው፤ የሩሲያ ኃይሎች ክሪሚያን ጨምሮ ከሁሉም የዩክሬን ግዛቶች ለቀው ካልወጡ ሀገራቸው ከሞስኮ ጋር እንደማትደራደር ተናግረዋል።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ጨምረውም የሰላም ስምምነቱ ከመጀመሩ በፊት ዩክሬን የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) አባል የመሆን ፍላጎቷን መተው አለባትም ብለዋል።

ፑቲን ለተኩስ አቁም ስምምነቱ ያስቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች የገለጹበትን መግለጫ ያወጡት ከ90 ሀገራት የተውጣጡ መሪዎች ትናንት ቅዳሜ በስዊዘርላንድ ተገናኝተው በዩክሬን ሰላም ላይ ለመምከር በዝግጅት ላይ ባሉበት ወቅት ነው። በዚህ ጉባኤ ላይ ሩሲያ አልተጋበዘችም።

ፑቲን አርብ ዕለት በሞስኮ ከሚገኙ አምባሳደሮች ጋር በነበራቸው ስብሰባ ላይ እንደተናገሩት፤ የዩክሬን መንግሥት በከፊል በሩሲያ ከተያዙት አራቱ ክልሎች ከዶኔስክ፣ ሉሃንስክ፣ ኼርሶን እና ዛፖሬዢያ ለቆ እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

ፑቲን ጨምረውም ዩክሬን የሩሲያን የጦር ግስጋሴ ለመግታት የኔቶን ወታደራዊ ጥምረት ለመቀላቀል የምታደርገውን ጥረት በይፋ ማቆም አለባትም ብለዋል።

“ኪዬቭ በእነዚህ ቅደመ ሁኔታዎች ላይ ውሳኔ ለማሳለፍ ዝግጁ ስትሆን በእኛ በኩል ወዲያውኑ ተኩስ እንዲቆም እና ድርድር እንዲጀመር ትዕዛዝ እናስተላልፋለን” ብለዋል ፑቲን።

የዩክሬን የፕሬዚዳንት አማካሪ ሚካኼሎ ፖዶልያክ ፑቲን ያቀረቡትን ቅድመ ሁኔታ “አሳፋሪ” ብለውታል።

አርብ ዕለት ፕሬዚዳንት ዜሌንስኪ ለጣልያኑ ስካይ ቲጂ24 ቴሌቪዥን ሲናገሩ “ይህ መልዕክት ሒትለር በመጨረሻው ሰዓታት ካደረገው ንግግር ጋር ተመሳሳይ ነው። ሒትለር በንግግሩ የቼኮዝላቫኪያን ክፍል ስጡኝ ብሎ ነበር” ብለዋል።

የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስትር ሎይድ ኦስቲን በበኩላቸው፤ ሩሲያ ያቀረበችውን ቅድመ ሁኔታ ውድቅ አድርገው፤ ፑቲን የዩክሬንን ሉዓላዊ ግዛት በሕገ ወጥ መንገድ ይዘዋል ሲሉ ከሰዋል ።

“ሰላም ለማምጣት በሚል ፑቲን ዩክሬንን ለመጨቆን ምንም ሥልጣን የለውም” ብለዋል።

የኔቶ ዋና ፀሐፊ የንስ ስቶልትንበርግ በበኩላቸው፤ ፑቲን ያቀረቡት ሃሳብ “በቅንነት የቀረበ አይደለም” ብለውታል።

የሩሲያ የፖለቲካ ተንታኝ ታቲያና ስታኖቫያ እንደሚሉት፤ የፑቲን ዕቅድ ስምምነት ላይ የማያደርሱ ጥያቄዎችን በማቅረብ የሰላም ንግግሩ ከመጀመሩ በፊት የንግግሩን ዋጋ ለማሳነስ ያለመ ነው።

ዜሌንስኪ ትናንት ቅዳሜ ዕለት የሚካሄደውን ጉባኤ የሚሳተፉ ሲሆን፣ ሰፊ ዓለም አቀፍ ድጋፍ እንደሚያገኙ ተስፋ አድርገዋል።

የጉባኤው ዓላማ በዓለም አቀፍ ሕግ እና በተባበሩት መንግሥታት ስምምነቶች መሠረት የዓለም መሪዎች ለዩክሬን ዘላቂነት ያለው ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ የመወያያ መድረክ መክፈት እንደሆነ የስዊዝ መንግሥት ገልጿል።

በዚህ ጉባኤ ላይ የአሜሪካ ምክትል ፕሬዚዳንት ካማላ ሐሪስ፣ የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን፣ የጀርመን መራሒ መንግሥት ኦላፍ ሾልዝ፣ የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ እና የአውሮፓ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት ኡርሱላ ቮን ደር ላይን ይሳተፋሉ።

ሩሲያ በጉባኤው ላይ ያልተጋበዘች ሲሆን፤ ቻይናም ጥሪ ቢቀርብላትም ሩሲያ ባልተገኘችበት ጉባኤ ላይ እንደማትሳተፍ ገልጻለች።

# ስፖርት



# የማይደክመው አቦሸማኔ

**አስማየሁ ግዛው**

ይህ ሰው ድል ያላደረገበት የውድድር መድረክ፣ ክብረወሰኖችን ያላስመዘገበበትን ቻምፒዮናዎች ፈልጎ ማግኘት ይከብዳል። በ 25 ዓመታት የሩጫ ሕይወቱ ኦሊምፒክንና የዓለም ቻምፒዮናን ጨምሮ በሁሉም መድረኮች ደጋግሞ መንገስ ችሏል። ስፖርት የእድሜ ስራ ነው የሚለውን ሃሳብ ውድቅ ካደረጉ ጥቂት ስፖርተኞች ተርታ የሚያሰልፈውን እንቅስቃሴውን አሁንም አጠናክሮ እንደቀጠለበት ነው።

የረጅም ርቀት አትሌቲክስ ንጉሱ ቀነኒሳ በቀለ፤ በስፖርቱ ዓለም አስደናቂ ስኬቶችን ከተጎናጸፉና ከተዘመረላቸው ስፖርተኞች መካከል አንዱ ሊሆን ችሏል። አትሌቲክስን ከጀመረበት ወቅት አንስቶ በርካታ ጀብዱዎችን በመፈጸም የስፖርት ቤተሰቡን ቀልብ ገዝቷል። በአስደናቂ አሯሯጡና አጨራረሱ የሚታወቀው አትሌት፣ ሀገሩን በብዙ መድረኮች ወክሎ ለማመን የሚከብዱ ድሎችንም አስመዝግቧል።


በረጅም ርቀት ሩጫ ለመቁጠር የሚያዳግቱ ሜዳሊያዎችን አጥልቋል። በኦሊምፒክ ጨዋታዎች 3 ወርቆችን፣ በዓለም ቻምፒዮና 5 ወርቆችን፣ በዓለም ሀገር አቋራጭ ቻምፒዮና 11 ወርቆችን እንዲሁም በትልልቅ የዓለም ማራቶን ውድድሮች 2 ወርቆችን የግሉ አድርጓል። በ25 ዓመታት የአትሌቲክስ ሕይወቱ 26 የወርቅ ሜዳሊያዎችን ወስዷል። በእነዚህ ዓመታት በዓለም አቀፍ ተሳትፎ ወርቅን ጨምሮ ከ30 በላይ ሜዳሊየዎችን በመሰብሰብ ምትሃተኛ አትሌት መሆኑንም አስመስክሯል። በመም ውድድሮች ያሳየውን የአሸናፊነት ብቃት በጎዳና ውድድሮችም መድገም የቻለው አንጋፋው አትሌት፣ ምንም እንኳን ጉዳት ቢፈትነውም እጅ ሊሰጥ ግን አልፈቀደም።

ጉዳት አቅሙን እስከ መጨረሻው አውጥቶ እንዳይጠቀም ቢያደርገውም ቅሉ በተሰለፈባቸው ውድድሮች ግን ለማመን የሚከብዱ ድሎችን በማስመልከት ተወዳጅነትን ማትረፍ ችሏል። በእድሜ አንጋፋ ቢሆንም አሁንም ስራውን ሳይታክት እየሰራ ይገኛል። በቅርብ ጊዜ በተካሄዱ ውድድሮች የአሸናፊነት መንፈሱ አብሮት እንዳለም አስመልክቷል።

ከቀናት በፊት 42ኛ ዓመቱን የደፈነው አትሌቱ አሁንም ከፊቱ ለሚጠብቀው ትልቅ የዓለም ድግስ ራሱን በማዘጋጀት ላይ ተጠምዷል። በጥቂት ወራት ልዩነት በተሳተፈባቸው ማራቶኖች ባስመዘገበው ውጤት ኢትዮጵያን በፓሪስ ኦሊምፒክ በሚወክለው ብሄራዊ ቡድን ውስጥ በመካተቱ የትኩረት ማዕከል መሆኑን ቀጥሏል። ብዙ ክብረወሰኖችን በማሻሻል እና ሜዳለያዎችን የግሉ በማድረግ የብርታትና የጥንካሬ ተምሳሌት በመሆኑ ‹‹አንበሳ›› የሚለው ቃል መጠሪያው ሆኗል።

ውጤታማው የረጅም ርቀት ሯጭ፣ የአትሌቶች መፍለቂያ ከሆነችው በቆጂ ወጥቶ ዓለምን ጉድ አሰኝቷል። የአትሌቲክስ ሕይወቱን የጀመረው ገና በለጋ እድሜው ሲሆን በአስደናቂ ጽናት እና ታታሪነት በአትሌቲክሱ ነግሷል። በዚህም በዓለም አትሌቲክስ ከታዩት የምን ጊዜም ምርጥ የረጅም ርቀት ሯጮች ግንባር ቀደሙ ነው።

የ5 ሺ እና የ10 ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰኖችን ከ15 ዓመታት በላይ በእጁ ቆይቷል። የማራቶን ምርጥ ሰዓትን 2 ሰዓት ከ1 ደቂቃ ከ41 ሴኮንድ ማስመዝገብም ሶስተኛው ፈጣን አትሌት ነው። በአሌቲክስ ከ120 በላይ ውድድሮችን ያሸነፈ ሲሆን ለቁጥር የሚታክቱ ሜዳሊያዎችንና ዋንጫዎችን በማሸነፍ በዓለም አቀፍ



ውድድሮችም በርካታ ድሎችን መጎናጸፍ ችሏል።

በሩጫ ዘመኑ ድንቅ ከሆኑ አትሌቶች ከባድ ፉክክር ቢገጥመውም ድንቅ አትሌት መሆኑን በተግባር ለዓለም ማስመስከር ችሏል። በተለያዩ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ አስደናቂ ድሎችን በመቀዳጀት ከምንጊዜውም የረጅም ርቀት ሯጮች አንዱ መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ።

አትሌቱ በመም ውድድሮች ካስመዘገበው አስደናቂ ስኬት በተጨማሪ በማራቶን የላቀ ውጤት በማስመዝገብ አሁንም ተስፋ እንዲጣልበት ማድረግ ችሏል። እኤአ በ2014ቱ የፓሪስ ማራቶን ውድድር 6ኛውን የማራቶን ፈጣን ሰዓት በ2፡05፡04 አሸንፏል። በርሊን ማራቶንን 2፡03፡03 በሆነ አዲስ የግል ምርጥ ሰዓት ሲያስመዘግብ፤ እአአ በ2019 እዚያው በርሊን ላይ ለዓለም ክብረወሰን እጅግ በቀረበ ሰዓት ድሉን ደግሞታል።

ቀነኒሳ በጉዳት ሳይሳተፍባቸው ከቀረባቸው መድረኮች በስተቀር ምርጥና የማይዋዥቅ ብቃቱን ለአትሌቲክስ ወዳጆች ማስኮምኮሙን ቀጥሏል። እድሜው አርባዎቹን ቢሻገርም በሚያስደንቅ ሁኔታ ላይ እንዳለ ተጨማሪ ድሎችን ለማስመዝገብ በጥረት ላይ ነው።

ቀነኒሳ ልደቱን ሲያከብር በፓሪስ ሀገሩን ወክሎ ሌላ ታሪክ ለመጻፍ የተለመደውን ዝግጅት እያደረገ ነው። የዓለም አትሌቲክስ የዓመቱ ምርጥ አትሌት፣ የትራክና የጎዳና ውድድሮች ምርጥ አትሌትና የኢትዮጵያ የዓመቱ በጎ ሰው የሚሉ ክብሮችን መቀዳጀት የቻለው ንጉሱ ታሪክን ለመጻፍ የአሸናፊነት መንፈሱን ይዞ የውድድሩን መጀመር ብቻ ይጠባበቃል።




# የኢድ አል አድሃ በዓል አከባበር

**እየሩስ ተስፋዬ**

ሠላም ልጆችዬ እንዴት ናችሁ? ሳምንቱን በተለያየ ሁኔታ እንዳሳለፋችሁ ይታወቃል። በተለይም የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ፈተና ወስዳችኋል አይደል? ፈተናው እንዴት ነበር? ጥሩ እንደነበር ተስፋ አደርጋለሁ።

ልጆችዬ ዛሬ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል የኢድ አል አድሃ ወይም አረፋ በዓል አንዱ እንደሆነ ይታወቃል። በዓሉን ለምታከብሩ ልጆች በእኛ በኩል ከወዲሁ እንኳን ለአረፋ በዓል አደረሳችሁ እና መልካም በዓል ማለት እንወዳለን።

ልጆችዬ የአረፋ በዓል ኢትዮጵያን ጨምሮ በመላው ዓለም በሚገኙ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥነ ስርዓቶች እና በተለያዩ ክዋኔዎች የሚከበር በዓል ነው። በአገራችንም የሃይማኖቱ ተከታዮች ወደ መስጅድ በመሄድ የሶላት ስግደት በመስገድ እና ሌሎች ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓቶችን በመከወን በዓሉን በደመቀ ሁኔታ ያከብሩታል።

ልጆችዬ የአረፋ በዓል ለምን እንደሚከበር ታውቃላችሁ? ‹‹አዎ›› ላላችሁ ልጆች ጎበዞች። ላማታውቁት ደግሞ ለምን የሚከበር መሰላችሁ? ነብዩ ኢብራሂም ልጃቸው እስማኤልን በአላህ ትእዛዝ ለመስዕዋት ሲያዘጋጁ በምትኩ ሙክት በግ መቅረቡን የሚያስታውስ በመሆኑ ‹‹የመስዋዕት በዓል›› ተብሎ ይከበራል። እናም በዚህ በዓል ያለው ለሌለው እያካፈለ በአብሮነት፣ በመረዳዳት እና በመተጋገዝ ያከበራል። የሃይማኖቱ መሪዎችዎችም የአረፋ በዓል እዝነት በተግባር የሚታይበት ሃይማኖታዊ በዓል ነው ይላሉ።

ልጆችዬ በበዓላት ወቅት አምሮና ደምቆ ማከበር የተለመደ ነው። አንዳንዶቹ በዓሉን አምረውና ደምቀው ለማክበር ለራሳቸውም ሆነ ለልጆቻቸው አዳዲስ



ልብሶችን በመግዛት አምረው ይታያሉ። በአቅም እና በሌሎች ምክንያቶች መግዛት ያልቻሉ ሰዎች ያላቸውን አልባሳት አጥበው እንዲሁም አሳምረው በዓሉን በደስታ ያከብሩታል።

አቅሙ የፈቀደለት አማኝ ደግሞ ለመስዋዕትነት የሚቀርቡ እንስሳትን በማረድና ለሌላቸው ወገኖች በማካፈል በዓሉን ያለምንም መከፋት ደስ ብሏቸው እንዲያከብሩት ያደርጋል። ልጆችዬ አቅም እስካለ ድረስ፤ አቅም የሌላቸውን ወይም አቅመ ደካማ የሆኑ ሰዎችን መርዳት ደስ ይላል አይደል? ‹‹ እንዴ በሚገባ›› እንዳላችሁኝ ምንም ጥርጥር የለኝም። እውነት ነው። ከችግር ውስጥ መውጣት የሚቻለው ያለንን እና አቅማችን የፈቀደውን በማካፈል እንዲሁም በመረዳዳት ነው።

ልጆችዬ የአረፋ በዓል ከሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት በተጨማሪ እንደየአካባቢው ባህልና ሁኔታ የተለያዩ ምግቦችን በማዘጋጀት አብሮ በመብላትና በመጠጣት ደስ ብሏቸው ያሳልፋሉ። በአገራችን በበዓላት ወቅት ቤተሰብ፣ ዘመድ፣ ጎረቤት ጓደኛን እና ሌሎችንም መጠየቅም የተለመደ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ በሥራ፣ በትምህርት እና በተለያዩ ምክንያቶች አሁን ከሚኖሩበት ቦታ ወደ ትውልድ ቀያቸው በመመለስ በዓሉን ከወላጆቻቸው፣ ከዘመድ አዝማድ፣ ከጎረቤተቻቸው እንዲሁም ከአብሮ አደግ ጓደኞቻቸው እና ከሌሎች ጋር በመሆን በጣም ደስ በሚል ሁኔታ ያከብሩታል። ልጆችዬ ሰብሰብ ብሎ በዓሉን ማክበር ደስ ይላል አይደል? እናንተም በዓሉን በደመቀ ሁኔታ እያከበራችሁ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለኝም።

ልጆችዬ የሃይማኖት አባቶች ሁሌም እንደሚመክሩት እንዲህ ያሉትን በዓላት በደስታ፣ በጋራ ሰብሰብ ብሎ በጨዋታ እና በደመቀ ሁኔታ ከማክበር በተጨማሪ አቅም የሌላቸውን ወገኖች፣ የታመሙ ሰዎችን፣ በጎዳና እና በተለያየ ሀኔታ ውስጥ ያሉ ሰዎችን መርዳት እንደሚገባ ይመክራሉ። እናንተም ከወላጆቻችሁ ጋር በመነጋገር የቻላችሁትን ብታደርጉ ፈጣሪያቹንም ችግረኞችንም አስደሰታችሁ ማለት አይደል?

ልጆችዬ ከበዓሉ ጋር ተያይዞ የምንላችሁ አለን። ምን መሰላችሁ? በበዓላት ወቅት ሁሌም እንደምንላችሁ በምትመገቡበት ወቅት ከመጠን በላይ መጥገብ የለባችሁም። ለምን? ካላችሁም እንዳትታመሙ በማሰብ ነው እንድትጠነቀቁ ነው እሺ። ልጆችዬ አሁን እንሰነባበት። ዛሬ በዓልም አይደል? የመልካም ምኞታችንን በድጋሚ እንግለጽ? በጣም ጥሩ። ለመላው የእስልምና እምነት ተከታይ ልጆች ሁሉ እንኳን ለአረፋ በዓል አደሳችሁ! መልካም በዓል እንዲሆንላችሁም ተመኘን!